# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ረቡዕ

83ኛ ዓመት ቁጥር 365 ጳጉሜን 5 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!







የኤ አይ ሰመር ካምፕ ተመራቂዎች

# አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለዛሬ ሳይሆን ለነገ መልካም ፍሬ የሚሰጥ ምርጥ ዘር ነው

ገጽ 4



## የኢትዮጵያዊነት ኅብር- የድልና የተስፋ ስንቅ

**መስከረም ሰይፉ**

**ዜና ሐተታ**

ኢትዮጵያን በልኳ የሚያውቋት በርካታ ብሔሮችን፣ ቋንቋዎችና ባህሎችን በአንድነት አሰባስባ የያዘች የጋራ ማዕድ መሆኗን ይመሰክራሉ። የጋራ መገለጫዋና ኅብሯ ደግሞ እንዲሁ በዋዛ ፈዛዛ የተገኘ አለመሆኑን ለሀገራቸው ሲሉ ደማቸውን ያፈሰሱ ጀግኖች ምስክር ናቸው።

ኢትዮጵያ የጀግንነት፣ የነፃነትና የእኩልነት ምልክት ሆና ስሟ እንዲነሳ ያደረጉ አባቶች በየአካባቢው አሉ። በዓድዋ ድል ኢትጵያውያን ሁሉ ልዩነታቸውን ወደ ኋላ በመተው አንድ

የኢትዮጵያዊነት... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ገመቹ አራርሳ ዶ/ር

## ድህነትን ለመሻር የተሰለፉ እጆች

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ትንታኔ**

ምድረ ቀደምት፣ የወርቃማ ድሎች ባለቤት፣ የጥቁር አርበኞች መኖሪያና በርካታ የተፈጥሮ ሀብቶችን የታደለችው ኢትዮጵያ በታሪኳ የሥልጣኔ ቁንጮ ላይ ወጥታለች፣ በቁልቁለት ጉዞም ወርዳ የድህነትን ወለል ረግጣለች፡፡ ዛሬ ላይ ኢትዮጵያ ለዘመናት ከተጫናት ድህነት ለመላቀቅ፣ ወደኋላ ከሚጎትቷት አለመግባባቶችና ግጭቶች ጥሳ ለመውጣት በትጋት ላይ ናት፡፡

ድህነትን ለመሻር... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# የብልጽግና ሞተር

**ማህሌት ብዙነህ**

ወጣቶች የሀገር ተረካቢ ብቻ ሳይሆኑ የሀገር ባለቤት ናቸው፡፡ ኢትዮጵያ ሳትፈርስ ለዘመናት የቀጠለችውም በተለያዩ ዘመናት የሚገኙ ወጣቶች በግንባር ቀደምትነት በተወጡት ሚና ነው፡፡

የተሻለች ሀገርን ለመገንባት የሁሉም ዜጋ አስተዋጽኦ አስፈላጊ ቢሆንም የወጣቱ ሚና ግን የላቀ እንደሆነ ይታመናል፡፡ በዚህም ለመጪው ትውልድ የበለጸገች ኢትዮጵያን ለመፍጠርና ለማስረከብ የዛሬ ወጣቶች በሀገራቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ላይ ትልቅ ሃላፊነት አለባቸው፡፡

ታዲያ ለነገዋ የበለጸገች ኢትዮጵያ ወጣቱ ትውልድ ምን ሃላፊነት አለበት፤ ምንስ ሚናዎችን መወጣት ይጠበቅበታል?

የአንድ ሀገር ወጣት "የትናንት ታሪክ አሻጋሪ፣ የዛሬ መሠረት፣ የነገ ሀገር ነው" የሚለው የኢትዮጵያ ወጣቶች ምክር ቤት የአደረጃጀት ዘርፍ ሃላፊ እና የአዲስ አበባ ወጣቶች ማህበር ዋና ጸሀፊ ወጣት ይሁኔ መሀመድ ነው።

አባቶች የትናንት መሠረት፣ ህጻናት የነገ ተስፋ ሲሆኑ ወጣቶች አሁን ናቸው ያለው ወጣት ይሁኔ ፤ በዚህም ታሪክን ከአባቶቹ ተሸካሚ እና ተቀባይ፤ የዛሬ መሠረት እና የነገ ሀገር ውጤት ወጣት ነው ብሏል፡፡


የአንድ ሀገር ወጣት ማለት በሀገሩ ውስጥ የነበሩ ችግሮችና እድሎች የሚያይና የሚገነዘብ ፣ ዛሬ ያለበትን ሁኔታ የሚረዳ እና ወደነገ መሻገር የሚገባቸውን ማሻገር ላይ ትኩረት አድርጎ የሚንቀሳቀስ ነው፡፡



ወጣት ይሁኔ መሀመድ

ወጣት ይሁኔ እንደሚለው ኢትዮጵያ በወጣቶች የተገነባች ታላቅ ሀገር ነች፡፡ ታሪክን መለስ ብለን ብናይም በጣሊያን ወረራ ቅኝ ግዛት ውስጥ ላለመውደቅ መስዋእት የከፈሉ ዛሬ አያት፣ ቅድመ አያቶቻችን የምንላቸው በጊዜው የነበሩ ወጣቶች ናቸው፡፡

በዚህም ካለምንም የዘርና ሃይማኖት መከፋፈል በአንድነት ተነስተው ቴክኖሎጂ ባልበለጸገበት ዘመን ኢትዮጵያዊነትና ነጻነት ተጠብቆ እንዲኖር መስዋእትነት የከፈሉት በዛን ዘመን የነበሩ ቆራጥ ወጣቶች መሆናቸውን ያብራራል፡፡



አቶ በላይ ንጉሤ

ከዛ በኋላም ባሉ ታሪኮች ሲታይ ኢትዮጵያን ከፍ አድርገው ያስቀጠሉ በየዘመኑ የነበሩ ወጣቶች ቆራጥነትና መስዋእትነት መሆኑን ተናግሯል፡፡

የሀገርን ሰላምና የህብረተሰብን አንድነት ጉዳት በመካስ ውስጥ እንዲሁም ያሉ ችግሮችን በማረም ውስጥ ትልቁን ኃላፊነት የሚሸከመው ወጣቱ ነው የሚለው ወጣት ይሁኔ፤ ሰላምን በመጠበቅ እውቀትንና ጉልበትን ማስረጽ በመቻል በበለጸገች ሀገር ውስጥ የተሟላ

የብልጽግና... ወደ ገጽ 4 ዞሯል






ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር)

## በ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና 5 ነጥብ 4 በመቶ ተማሪዎች 50 በመቶና ከዚያ በላይ ውጤት አስመዘገቡ

- **አንድ ሺህ 363 ትምህርት ቤቶች አንድም ተማሪ ማሳለፍ አልቻሉም**

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በ2016 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ከወሰዱ 674 ሺህ 823 ተማሪዎች ውስጥ 36 ሺህ 409 ተማሪዎች 50 በመቶና ከዚያ በላይ ውጤት ማስመዝገባቸውን ትምህርት ሚኒስቴር አስታወቀ፡፡

የትምህርት ሚኒስትሩ ብርሃኑ ነጋ (ፕ/ር) ትናንት በሰጡት መግለጫ እንዳሉት፤ በ2016 ዓ.ም የ12ኛ ክፍል ሀገር አቀፍ ፈተና ከወሰዱ 674 ሺህ 823 ተማሪዎች ውስጥ 36 ሺህ 409 ተማሪዎች የማለፊያ ነጥብ አምጥተዋል፡፡ ይህም የአጠቃላይ ተፈታኞችን 5 ነጥብ 4 በመቶ ይሸፍናል፡፡

የማለፊያ ውጤት ያስመዘገቡ ተማሪዎች ቁጥር ከባለፈው ዓመት ተመሳሳይ ጊዜ በ 9 ሺህ 114 ተማሪዎች ብልጫ እንዳለውም ገልጸዋል።

በተፈጥሮ ሳይንስ ዘርፍ 28 ሺህ 158 ወይም 9 በመቶ በማህበራዊ ሳይንስ ደግሞ 8 ሺህ 251 ወይም 2 በመቶ የማለፊያ ውጤት ማምጣታቸውን አመላክተው፤ አንድ ሺህ 221 ተማሪዎች ከፍተኛ ውጤት አስመዝግበዋል ብለዋል፡፡

ቀደም ሲል በነበረው የመሰናዶ ትምህርት በትግራይ ክልል ፈተናቸውን ከወሰዱ ተፈታኞች መካከል ከ700 በተፈጥሮ ሳይንስ ከትግራይ ቀላሚኖ ትምህርት ቤት አንድ ተማሪ 675 ማስመዝገቡን ገልጸዋል።

በተመሳሳይ በዚህ ዓመት ፈተናቸውን ከወሰዱ ተማሪዎች መካከል ከ600 በተፈጥሮ ሳይንስ ከአዲስ አበባ አግዚሊየም ካቴድራል ትምህርት ቤት 575 (በሴት ተማሪ) የተመዘገበ መሆኑን ጠቅሰው፤ በማህበራዊ ሳይንስ ከአዲስ አበባ ኢትዮ ፓረንትስ 538 (በሴት ተማሪ) ከፍተኛ ውጤት መመዝገቡን ተናግረዋል ።

በዚህ ዓመት ሁሉም ክልሎችና ከተማ መስተዳድሮች ከአምናው በተሻለ ተማሪዎችን ማሳለፋቸውን የገለጹት ሚኒስትሩ፤ አንድ ሺህ 363 ትምህርት ቤቶች ግን ምንም ተማሪ አለማሳለፋቸውን ጠቁመዋል።

50 በመቶና ከዚያ በላይ ያመጡት በቀጥታ ወደ ዩኒቨርሲቲ እንደሚገቡ የጠቆሙት ፕሮፌሰር ብርሃኑ፤ የተወሰኑ ተማሪዎችም በሪሜዲያል ፕሮግራም ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ጨምረው ገልጸዋል።

# ሶማሊያውያን የራሳቸው ያልሆነ ጦርነት ወደ ሀገራቸው ከመጋበዝ እንዲቆጠቡ ጥሪ ቀረበ

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- ሶማሊያውያን የራሳቸው ያልሆነ ጦርነትን ወደ ሀገራቸው ከመጋበዝ እንዲቆጠቡ የሶማሌ ክልል የሀገር ሽማግሌዎች ጥሪ አቅርበዋል፡፡ የሶማሊያ ክልል የሀገር ሽማግሌዎችና የህብረተሰብ ተወካዮች በአፍሪካ ቀንድ እየተስተዋሉ ባሉ ወቅታዊ ጉዳዮች ዙሪያ ውይይት አካሂደዋል፡፡

ውይይቱን የመሩት የሶማሌ የሀገር ሽማግሌና የጎሳ መሪው ገራድ ኩልሚዬ ገራድ መሀመድ እንደገለጹት፤ የሀገርን ብሔራዊ ጥቅም የማስከበር ጉዳይ ዋነኛ አጀንዳ ነው፡፡ ጎረቤት ሶማሊያውያን የራሳቸው ያልሆነ ጦርነት ወደ ሀገራቸው በመጋበዝ የአፍሪካ ቀንድ ቀጣናን ወደ ቀውስ ማስገባት የለባቸውም፡፡

እንደ ገራድ ኩልሚዬ ገራድ መሀመድ ገለጻ፤ ኢትዮጵያን የሚጎዳ ሁሉ የሶማሌ ክልል ሕዝብ ጉዳት ነው፡፡ ከሌሎች ሕዝቦች ጋር በመሆን የሀገርን ጥቅም ለማስከበር ይሠራል። ኢትዮጵያ የባህር በር የማግኘት መብቷን ለማረጋገጥ የምትሠራቸውን ሥራዎች የሶማሌ ክልል ሕዝብ እንደሚደግፍም ገልጸዋል፡፡

የተለያዩ ሃይሎች ወደ ሶማሊያ መጥተው የአፍሪካ ቀንድን ለማበጣበጥ የሚያደርጉትን እንቅስቃሴም እንቃወማለን ያሉት ገራድ ኩልሚዬ፣ በሶማሊያ ያሉ የተለያዩ ሃይሎች ለሶማሊያ ሕዝብ ጥቅም ብለው ሳይሆን ጦርነት በመክፈት ችግር የመፍጠር ዓላማ ያላቸው መሆናቸውን በመገንዘብ ሕዝቡ ሊቃወማቸው እንደሚገባም ተናግረዋል።

የሶማሌ ክልል ሕዝብንና የሶማሊያ ሕዝብን ድንበር ቢለያቸውም ወንድማማቾች ናቸው ያሉት የጎሳ መሪው፤ የአብሮነት ታሪካቸውን ሊጠብቁት ይገባል ብለዋል።

የባህር በር ጥያቄው አብሮ ለማደግ የሚረዳ እንጂ የሚያራርቅ አጀንዳ አይደለም ያሉት የሀገር ሽማግሌዎቹ፤ የኢትዮጵያ ጠላቶች ላለፉት 40 ዓመታት የሶማሊያ ሕዝብ ሲቸገር አላስታወሱትም፣ ከሽብር ጥቃትም አላዳኑትም፡፡ ዛሬም ከአልሻባብ ጋር ለመዋጋት ፍላጎት የሌላቸው በመሆኑ የሶማሊያ ሕዝብ ሊቃወማቸው ይገባል ብለዋል።

የኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት ለሶማሊያ ባለውለታ መሆኑን የጠቆሙት የሀገር ሽማግሌው፤ የሶማሊያ መንግሥትም ውሳኔውን እየተቃወሙ ያሉ ሕዝቦችን ሊያደምጥ ይገባዋል ብለዋል፡፡

የሀገር ሽማግሌው እንደገለጹት፤ በአሁኑ ጊዜ ከ500 ሺህ በላይ የሶማሊያ ስደተኞች በኢትዮጵያ ይኖራሉ፡፡ እንዲሁም ባለፉት 40 ዓመታትም በሚሊዮን የሚቆጠሩ ስደተኞች መጠለያቸውን ኢትዮጵያ አድርገው ሀብት አፍርተው እየኖሩ ነው፡፡ በአዲስ አበባና በጅግጅጋ ዩኒቨርሲቲዎች በርካታ ሶማሊያውያን በኢትዮጵያ መንግሥት ድጋፍ እየተማሩ ነው፡፡

የሶማሊያ ሕዝብ ውለታ መላሽ ነው ያሉት ገራድ ኩልሚዬ ገራድ መሀመድ፤ ጥቂት ግለሰቦች ሥልጣንን ተገን በማድረግ ወንድማማች ሕዝቦችን ጠላት ለማስመሰል እየሞከሩ ነው፡፡ ይህ አይሳካላቸውም፤ ሕዝቡም እየተቃወማቸው ነው፡፡ ከሀገራቸው የኢትዮጵያን መውጣት አይፈልጉም፡፡ የኢትዮጵያና የሶማሊያ ሕዝብ ሽብርተኝነትን አብሮ ተዋግቷል፤ በሁለቱ ሰላም ወዳድ ሕዝቦች መካከል ችግር የሚፈጥር የውጭ ሃይልን መቃዎም ይገባል ብለዋል፡፡

ሌላኛው የሀገር ሽማግሌ ኡጋዝ አሊ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ሶማሊያ ከሩቅ ሀገራት ይልቅ ከጎረቤቶቿ ጋር በመወያየት የሚፈጠሩ ችግሮችን ሰላማዊ በሆነ አግባብ ልትፈታ ይገባል፡፡ ከውጭ የሚመጡ ኃይሎች የኢትዮጵያንና የሶማሊያን ጉርብትና ከማበላሸት ያለፈ ዓላማ አይኖራቸውም ያሉት ኡጋዝ አሊ፤ ሶማሊያውያን ችግር ሲገጥማት ቀድማ የምትደርሰው ኢትዮጵያ በመሆኗ በሀገራቸው የሚደረግ የጦርነት ቅስቀሳን መቃወም አለባቸው ብለዋል፡፡ የሶማሊያና ኢትዮጵያ ሕዝቦች የአፍሪካ ቀንድን በእጅ አዙር ችግር ውስጥ ለማስገባት የሚጥሩ ኃይሎች በመከላከል ረገድ አንድነታቸውን ሊያጠናክሩ ይገባል ሲሉም አሳስበዋል፡፡

# ሚኒስቴሩ ለመቄዶንያ የዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረገ

**አማን ረሺድ**




ካሳሁን ጎፌ(ዶ/ር)

አዲስ አበባ፡- የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስቴርና ተጠሪ ተቋማት የህብር ቀንን በማስመልከት ለመቄዶንያ የአረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን መረጃ ማዕከል የዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር ድጋፍ አደረጉ፡፡ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱና ተጠሪ ተቋማት "አብረን ነበርን፤ አብረን እንኖራለን" በሚል መሪ ሃሳብ የኅብር ቀንን አስመልክተው በትናትናው ዕለት በማዕከሉ ማዕድ አጋርተዋል፡፡

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ካሳሁን ጎፌ (ዶ/ር) በወቅቱ እንደተናገሩት፤ ሚኒስቴሩ ከተጠሪ ተቋማት ጋር በመሆን ማዕድ ማጋራትን ጨምሮ ከዘጠኝ ነጥብ አምስት ሚሊዮን ብር በላይ ድጋፍ አድርገዋል።

እንደ ሀገር የመስጠት ልምምድ ሊኖር እንደሚገባ የገለጹት ካሳሁን (ዶ/ር ፤ በመስጠት የሚጎል ነገር የለም ስለማይኖር ሁሌም መስጠትን ማስቀደም ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

ሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ በተለያዩ ጊዜ ድጋፍ ማድረጉን አውስተው፤ ዜጎች እንዲሁም ተቋማት የመረዳዳት ባህልን ማዳበር እንደሚገባቸው ገልጸዋል፡፡

በተጨማሪም በሀገር አቀፍ ደረጃ ጳጉሜን አራት የሚከበረውን የህብር ቀንን በማስመልከት በማዕከሉ ለሚገኙ አረጋውያንና የአእምሮ ህሙማን ማዕድ አጋርተዋል።

ለአረጋውያን ማዕድ ማጋራት ዘርፈ ብዙ ጥቅም ስላለው ሁሉም ዜጋ የአቅሙን መደገፍ እንደሚገባው አውስተው፤ ሚኒስቴሩ በየዓመቱ ጳጉሜን አራት በማዕከሉ ማዕድ ለማጋራት መወሰኑንም ገልጸዋል።

ሚኒስቴሩ በማዕከሉ ማዕድ ሲያጋራ የመጀመሪያው አለመሆኑን ገልጸው፤ ድጋፉ ተጠናክሮ ይቀጥላል ብለዋል።

የንግድና ቀጣናዊ ትስስር ሚኒስትር ዲኤታ ያስሚን ውሃቢረቢ በበኩላቸው፤ በተለያዩ ምክንያቶች ሕይወታቸውን በጎዳና ላይ ያደረጉ የህብረተሰብ ክፍሎችን በመደገፍ እራሳቸውን እንዲችሉና ለሌሎች እንዲተርፉ ማድረግ እንደሚስፈልግ ተናግረዋል፡፡

ድጋፉ በህብር፣ በመተባበር እንዲሁም አብሮ በመቆም ቀን መደረጉ ትልቅ ትርጉም እንዳለው አውስተው፤ ኢትዮጵያውያን ሁሌም መደጋገፍን ሊያስቀድሙ እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

የማዕከሉ መሥራችና ሥራ አስኪያጅ ቢኒያም በለጠ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ለተደረገላቸው ድጋፍ አመስግነው ሌሎች መሥሪያ ቤቶች ከዚህ ትምህርት በመውሰድ ድጋፍ እንዲያደርጉ ጠይቀዋል።

ማዕከሉ በአሁኑ ወቅት ከአዲስ አበባ ውጪ በተለያዩ ክልሎች አገልግሎቱን በማስፋት ደጋፊ ያጡ አረጋውያን እና የአእምሮ ህሙማን ወገኖቻችን በመሰብሰብ እንክብካቤ ለማድረግ በስፋት በመንቀሳቀስ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

በማዕከሉ ከሰባት ሺህ 500 በላይ አረጋውያንና የአዕምሮ ሕሙማን አገልገሎት እያገኙ መሆኑን ጠቅሰው፤ ወደ ማዕከሉ በመምጣት፣ በ8161 አጭር የጽሑፍ መልዕክት በመላክ እንዲሁም በጎ-ፈንድሚ ሁሉም ዜጋ ድጋፍና እገዛ እንዲያደርግ ጠይቀዋል።

ዜና



“የምናጋራው ማዕድ ብቻ ሳይሆን ለወገኖቻችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት ጭምር ነው”

- ከንቲባ አዳነች አቤቤ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- የምናጋራው ማዕድ ብቻ ሳይሆን ለወገኖቻችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት ጭምር ነው ሲሉ የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ አዳነች አቤቤ ገለጹ። የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትናንት ከ500 ሺህ በላይ ለሚሆኑ የመዲናዋ ነዋሪዎች ማዕድ አጋርቷል።

በእለቱ ከንቲባ አዳነች አቤቤ እንደተናገሩት፤ ማዕድ የምናጋራው አቅመ ደካሞች እና የሀገር ባለውለታዎች እንዲሁም አነስተኛ ገቢ ያላቸው የመንግሥት ሠራተኞች አዲሱን ዓመት በደስታ እንዲቀበሉ ለማድረግ ነው። በዚህም የምናጋራው ማዕድ ብቻ ሳይሆን ለወገኖቻችን ያለንን ፍቅርና አክብሮት ጭምር ነው ብለዋል።

ማዕድ የማጋራቱ ተግባር በሁሉም ክፍለ ከተማዎች እንደሚከናወን የገለጹት ከንቲባ አዳነች፤ ከከተማችን ልማት ሁሉም ተቋዳሽ እንዲሆን ለማድረግ እየጣርን ነው ብለዋል፡፡ ለመዲናዋ ነዋሪዎች ያለንን ክብር ለመግለጽ እና ለማሳየት ሁል ጊዜ ታትረው እንደሚሰሩም ገልጸዋል።

አዲሱ ዓመት የሀገር ባለውለታ መሆናችሁን ታሳቢ አድርገን እንደምናገለግላችሁ የምናሳይበት ነው ያሉት ከንቲባዋ፤ በኅብር ሆነን በርካታ ፈተናዎችን ተሻግረን ድል አስመዝግበናል። ከዚህ ውስጥ ጠያቂና ደጋፊ የሌላቸውን ወገኖች ዝቅ ብለን በማገልገል የማዕድ ማጋራት፣ የመኖሪያ ቤት አቅርቦት እና በኑሮ ውድነት የተፈጠሩ ጫናዎችን የማቃለል ሥራዎች እየተከናወኑ መሆኑን ተናግረዋል።

በበጎ ፈቃድ ሥራዎቻችን የነዋሪውን እርስ በእርስ የመደጋገፍ እና የመረዳዳት ባህል እንዲጎለብት እያደረግን ነው ያሉት ከንቲባ አዳነች፤ በዚህም የበለጠ ሀገራችሁን እየባረካችሁ መጪው ትውልድ የበለፀገች ሀገር መረከብ እንዲችል እንዲሁም ፈጣሪ እንዲረዳን የእናንተ ደስታ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

በዓሉ የሰላም፣ የፍቅርና የበረከት ይሁንልን በማለት ለሁሉም የኢትዮጵያ ሕዝብ የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት አስተላልፈዋል።

የመንግሥትን የሰው ተኮር ፖሊሲ፣ አቅጣጫ እና ጥሪ በመቀበል ሠርተው ካገኙት ለወገኖቻቸው ማካፈልን ባሕል ላደረጉ የከተማችን ልበ ቀና ባለሀብቶች እና በጎ ፈቃደኞች እንደሁልጊዜው ሁሉ መስጠት አያጎድልምና ለወገኖቻችሁ ለምታደርጉት በጎነት ሁሉ በራሴና በከተማ አስተዳደሩ ስም አመሰግናለሁ ብለዋል።

# የአፍሪካ ከተሞች የቃልኪዳን ሰነድ

ቃልኪዳን አሳዬ



ፎቶ በረሁን ታደሰ

አቶ ጃንጥራር ዓባይ



አናክላውዲያ ሮዝባች



ወይዘሮ ጫልቱ ሳኒ

ከከተሞች መስፋፋትና ፈጣን ዕድገት ጋር ለተያያዙ ተግዳሮቶች ወጥ የሆነ መፍትሔ መከተል እና ከአጋር አካላት ጋር በትብብር መሥራት አስፈላጊ መሆኑ ይነሳል፡፡ እንዲሁም ከተሞችን ማዘመንና ዘላቂ ዕድገት ያላቸው በማድረግ የበለፀጉ ከተሞችን በመገንባት ሁሉንም ተጠቃሚ ማድረግ የትብብር ሥራ የሚሻ መሆኑ አያጠያይቅም፡፡

በአሁኑ ወቅት በርካታ የአፍሪካ ከተሞች የንጹህ መጠጥ ውሃ፣ የመብራትና ሌሎች መሠረተ ልማቶችን በአግባቡ ማግኘት እየቻሉ አይደለም፡፡ በተጨማሪም በአህጉሪቱ የከተማ ነዋሪ ዜጎች ቁጥር ከጊዜ ወደ ጊዜ በእጥፍ እየጨመረ መምጣቱ ይነገራል፡፡

ለዚህም በከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴርና በአፍሪካ ሕብረት አዘጋጅነት "ዘላቂ የከተሞች ልማት ለአፍሪካ ትራንስፎርሜሽን አጀንዳ 2063" በሚል መሪ ሃሳብ የመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም በአዲስ አበባ ከተማ ተካሂዷል።

በፎረሙ ማጠቃለያ የአፍሪካ ከተሞች ክትመት የቃልኪዳን ሰነድ የጸደቀ ሲሆን፤ የቃልኪዳን ስምምነቱ ከተሞች የሀገራት ኢኮኖሚ ማዕከል እና የብልፅግና መሠረት በመሆናቸው፣ በዕቅድና በሥርዓት የሚመሩ፣ ለኑሮ የተመቹና በቴክኖሎጂ የበለጸጉ ዘላቂ ከተሞችን ለመገንባት በማስፈለጉ እንደሆነ ተጠቅሷል።

የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስትር ጫልቱ ሳኒ እንደሚገልጹት፤ በኢትዮጵያ የተካሄደው የመጀመሪያው የአፍሪካ ከተሞች ፎረም ታሪካዊና ስኬታማ ነበር፤ ዘርፈ ብዙ ጥቅሞች ያሉት ነው፡፡ በዚህም ከ49 የአፍሪካ ሀገራት፣ የዘርፉ የሥራ ሃላፊዎች፣ የዓለም አቀፍ አጋር ድርጅት ተወካዮች፣ ምሁራንና የፋይናንስ ተቋማት ሃላፊዎችን ጨምሮ በፎረሙ ከ2 ሺህ በላይ ዜጎች ታድመውበታል፡፡

የአፍሪካ ክትመት ቃልኪዳን ሰነድ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ማዕከል የሆኑ ከተሞችን ማዘመንና ዘላቂ ዕድገት ለማረጋገጥ የሚያስችል እንደሆነ የሚያነሱት ሚኒስትሯ፤ ፍትሃዊ የሆኑ የከተማ ልማት ሥራዎች አስገዳጅ እንዲሆኑ በማድረግ ከተሞችን ለሀብታም ብቻ ሳይሆን ሁሉም ዜጎች መሠረተ ልማቶችን የሚቋደሱበትና አካታችነት ያለውን ልማት የሚያበረታታ ነው ይላሉ፡፡

የቃልኪዳን ሰነዱም ፈጣን ምጣኔ ባለው የአፍሪካ ክትመት ሂደት ሁሉንም አፍሪካዊ ተጠቃሚ እንዲሆን በትብብር ለመሥራት የሚያስችል ይዘት አካቷል፡፡ ከተሞችን በክላስተር በማደራጀት እንደየነባራዊ ሁኔታቸው የማደግ አቅማቸው ልክ በጋራ ማደግ እንደሚጠበቅባቸውና ይህንን የሚደግፍ መሆኑን ሚኒስትሯ ይናገራሉ፡፡

እንደ ሚኒስትሯ ገለጻ፤ በልማት አፍሪካውያን ወደኋላ የቀሩ በመሆናቸው አጀንዳቸውን የጋራ አድርገው በዓለም መድረኮች ላይ ድምጻቸውን ካላስተጋቡ ተደማጭነት አይኖራቸውም፡፡ በዚህም ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ የጸደቀው አዋጅ እንደሕግ ሆኖ ይቀጥላል፡፡ ይህንንም ተግባራዊ በማድረግ የትኛውም ዓለም አቀፍ ተቋም የሚያመጣቸው ሀብቶች በፍትሃዊነት ይሰራጫሉ፡፡

የዓለም የከተሞች ፎረም ከወራት በኋላ በግብጽ ካይሮ ይካሄዳል፤ ኢትዮጵያ ይህን ፎረም በማስተናገዷ ብዙ ልምዶች ማግኘቷን የሚጠቁሙት ሚኒስትሯ፤ በቀጣይም ከ20ሺህ በላይ ዜጎች የሚታደሙበትን የዓለም የከተሞች ፎረም ማዘጋጀት እንድትችል ጥረት እንደሚደረግ አመላክተዋል።

የአዲስ አበባ ከተማ ምክትል ከንቲባ ጃንጥራር ዓባይ በበኩላቸው፣ ፎረሙ ትርጉም ያላቸው ውይይቶች፣ ተሳትፎዎች እና የልምድ ልውውጦች በመሪዎች መካከል የተካሄዱበት እንዲሁም መሪዎቹ ተሻጋሪ እሳቤዎቻቸውን ለአፍሪካ የከተሞች ፎረም ዲክላሬሽን ግብዓትነት ያቀረቡበት ነው። ይህ አዋጅ ሰነድ ብቻ አይደለም፤ ለሁሉም አፍሪካውያን ብሩህ ተስፋ ለመቅረጽ ያለንን የጋራ ቁርጠኝነት የምናሳይበት ቃልኪዳናችን ነው ብለዋል።

የከተሞች መስፋፋት ማኅበራዊ እንቅስቃሴን ለማነቃቃት፣ ኢኮኖሚያዊ ዕድገትን እና ዘላቂ ልማትን ለማምጣት እምቅ አቅም እንዳለው የሚገልጹት አቶ ጃንጥራር፤ ይህን አቅም ለመጠቀም ግን ከቃላት ባለፈ የጋራ ግቦችን ለማሳካት ተግባርን፣ ትብብርን እና ያልተቋረጠ ቁርጠኝነትን እንደሚጠይቅ ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ ጃንጥራር ገለጻ፤ የመኖሪያ ቤት እጥረት፣ የአካባቢ መራቆት፣ የመሠረተ ልማቶች አለመሟላት፣ ኢኮኖሚያዊ ኢ-ፍትሐዊነትን የመሳሰሉ ተግዳሮቶች የምንጋራቸው ናቸው። በጋራ በመሥራት፣ ልምዶችን በመለዋወጥ እና እርስ በእርስ በመማማር እነዚህን ተግዳሮቶች መሻገር እንችላለን።

የከተሞቻችን እድገት ከገጠር ማህበረሰባችን ደህንነት ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው። ከተሞች ሁሉን አቀፍ እድገት ላይ በማተኮር የተሻሻሉ መሠረተ ልማቶችን፣ አገልግሎቶችንና ኢኮኖሚያዊ ዕድሎችን በመፍጠር የከተሞች መስፋፋትን ዕድል በማድረግ ወደ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ ብልጽግናና ዘላቂ ልማት ለመለወጥ በጋራ ልንሠራ ይገባል፡፡ ገጠራማ አካባቢዎቻችንም በዚህ ጉዞ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ ማስቻል ይጠበቅብናል ይላሉ አቶ ጃንጥራር።

እንደ ምክትል ከንቲባው ንግግር፤ በአዋጁ ውስጥ ከተዘረዘሩት መርሆች እና ከተቀመጡ ግቦች በላይ መሥራት የእያንዳንዳችን ቀዳሚ ተግባር ነው። የከተሞች መስፋፋት ለሁሉም አፍሪካውያን ጥሩ የእድገት አንቀሳቃሽ ኃይል እንዲሆን ከድንበር ተሻግረን መሥራታችንን መቀጠል አለብን።

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የሰፈራ ፕሮግራም ዋና ዳይሬክተር አና ክላውዲያ ሮዝባች በበኩላቸው እንደሚገልጹት፤ እ.አ.አ በ2016 በኢኳዶር በተካሄደው አዲሱ ዓለም አቀፍ የከተሞች አጀንዳ ሶስት መሠረታዊ ጉዳዮች ተነስተዋል። እነኝህም ዜጎችና መኖሪያ ቤት በከተማ ማዕከላት፣ መንግሥት ከተሜነትን የሚደግፍ አሳታፊና እስቲራቴጅካዊ አሠራር ተግባራዊ ማድረግ እንዳለበት፣ መሬትን የሥነምህዳርና ማህበራዊ ሁኔታዎችን ከግምት ውስጥ በማስገባት መገልገል ይጠበቃል።

እንደ ዋና ዳይሬክተሯ ገለፃ፤ 50 በመቶ የሚሆነው የአፍሪካ ሕዝብ በቂ የኤሌክትሪክ፣ የውሃና ሌሎች የመሠረተ ልማት አገልግሎቶችን በአግባቡ እያገኘ አይደለም፡፡ እንዲሁም በእርስ በእርስ ግጭት፣ ከአየር ንብረት ለውጥና ከሌሎችም ተግዳሮቶች ጋር ተያይዞ በርካታ ዜጎች ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል፡፡

በ2050 በአፍሪካ 60 ሚሊዮን አዲስ የከተማ ነዋሪዎች ይፈጠራሉ። ለዚህ ያለንን ሀብት በዋናነትም መሬትን በአግባቡ በመጠቀም፣ ተፈጥሮን በማክበርና ቅርሶችን በመጠበቅ ከተሞቻችንን መገንባት አለብን ያሉት ዋና ዳይሬክተሯ፤ ለዚህም አዲሱ ዓለም አቀፍ የከተሞች አጀንዳ አዳዲስ እሳቤዎች ተግባራዊ እንዲደረጉ በማነሳሳት በከተሞች ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲመጣ እያደረገ ይገኛል፤ ይህም ለአፍሪካውያን ተሞክሮ ሊሆን የሚችል እንደሆነ ይጠቁማሉ።

አሁን ባለው ሁኔታ ከተሞች እነኚህን ዜጎች ተቀብሎ የማኖር አቅም የሌላቸው በመሆኑ በተለይም የመሠረተ ልማትና መሠረታዊ አገልግሎቶችን መስጠት የሚችሉ ከተሞች በፍጥነት መገንባት እንዳለባቸው አንስተው፤ አፍሪካውያን ያላቸውን መልካም ተሞክሮች በመቀያየርና የመበልጸግ አቅማቸውን በአግባቡ መጠቀም እንዳለባቸው ይናገራሉ፡፡

በአሁኑ ወቅት በርካታ የዓለም ከተሞች ለዜጎች የሚሆን የመኖሪያ ቤት እጥረት እያጋጠማቸው በመሆኑ ሀገራት በዚህም ዘርፍ በትኩረት በመሥራት የዜጎችን ማህበራዊና ኢኮኖሚያ ችግሮችን ማቃለል እንዳለባቸው ዋና ዳይሬክተሯ ጥሪ አቅርበዋል።

## ብዝሃነትን የሚያከብር እውነተኛ ህብረ ብሄራዊ የፌዴራል ሥርዓት እየተገነባ ነው

መስከረም ሰይፉ



አቶ አገኘሁ ተሻገር



አቶ ብናልፍ አንዷለም

አዲስ አበባ፡- ብዝሃነትን የሚያከብር እውነተኛ ህብረ-ብሄራዊ የፌዴራል ሥርዓት እየተገነባ መሆኑን የፌዴሬሽን ምክር ቤት አፈ ጉባኤ አገኘሁ ተሻገር ገለጹ፡፡

የህብር ቀን የተለያዩ የህብረተሰብ ክፍሎችና የመንግሥት የሥራ ሃላፊዎች በተገኙበት «ኅብራችን ለሰላማችን» በሚል መሪ ቃል በብሄራዊ ቲያትር በትናንትናው እለት ተከብሯል፡፡

የፌደሬሽን ምክር ቤት አፈጉባኤ አገኘሁ ተሻገር እንደገለጹት፤ በህብረ ብሄራዊነታችን ውስጥ ያለው አንድነት ላለፉት በርካታ ዘመናት ሀገሪቷን ከፈተናዎች ጠብቆ ሉዓላዊነቷን አስከብሮ አቆይቷል፡፡

ህብራችንን ለአካታች ብልፅግና እና ዘላቂ ሠላም ለመጠቀም አበክሮ መሥራት ይጠበቃል ያሉት አቶ አገኘው ብዝሃነትን የሚያከብር እውነተኛ ህብረ-ብሄራዊ የፌዴራል ሥርዓት እየተገነባ ይገኛል ብለዋል፡፡

በአባቶቻችን ዘመን ኢትዮጵያዊ ማንነት በመኖሩ የሀገርን ሉዓላዊነትን አስጠብቆ ኢትዮጵያን የነጻነት ቀንዲል ማድረግ ተችሏል ያሉት አፈጉባኤው በአሁኑ ሰአትም የውጭም የውስጥም ጠላቶች ብዝሃ ማንነታችንን እንደ ግጭት መነሻ ለማድረግ ቢጥሩም ብሄራዊ ማንነት ያለው ሕዝብ በመሆኑ ሳይሳካላቸው መቅረቱን ገልጸዋል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የሀገሪቱ ህብር የዘመናት የአርበኝነት ውጤት መሆኑን አውቆ ለሀገሪቱ ሠላምና ሉዓላዊነት ከመቼውም ጊዜ በላይ አንድነታችንን ልናጠናክር ይገባል ብለዋል፡፡

አቶ አገኘሁ፤ ሀገር በአንድ ወገን ብቻ አትሠራም ያሉ ሲሆን ሁሉም በጋራ ሀገሩን ወደፊት ለማራመድ መቆም እንደሚኖርበት መክረዋል፡፡

የሰላም ሚኒስትር ብናልፍ አንዱአለም በበኩላቸው የህብር ቀን ሲታሰብ ባለ ብዙ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ባህል ፣ብሄርና መሰል የበርካታ ማንነት ህብር የሆነችው ኢትዮጵያ ትታሰባለች ብለዋል።

ሚኒስትሩ ህብራችን የውበታችን፣ የህለውናችን፣ ለሰላማችን መሠረት ነው ያሉ ሲሆን ኢትዮጵያውያን በርካታ ልዩነቶች ቢኖሯቸውም በብሄራዊ ማንነታቸው አንድ ሆነዋል ብለዋል።

ባለፉት ዓመታት ብዝሃነታችን ለድላችን ምክንያት እንደሆነው ሁሉ የሀገሪቱን ሰላምና መረጋጋት የማይፈልጉ ሃይሎች ደግሞ የግጭት ማስነሻ አድርገውት ቆይተዋል ያሉ ሲሆን ነገር ግን ኢትዮጵያዊነት የሁሉም የጋራ ማንነት መሆኑን መገንዘብና ለዛ መሥራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመዋል፡፡

ሚኒስትሩ በ2016 እንደሀገር ካሳለፍናቸው ፈተናዎች በመማር አዲሱን ዓመት መልካም ለማድረግ መሥራት ይገባል ያሉ ሲሆን ብዝሃነታችን ጸጋችን መሆኑን በመገንዘብ ብሄራዊ ማንነትን መገንባት ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባ ጠቁመዋል፡፡

# አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለዛሬ ሳይሆን ለነገ መልካም ፍሬ የሚሰጥ ምርጥ ዘር ነው

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለዛሬ ሳይሆን ለነገ መልካም ፍሬ የሚሰጥ ምርጥ ዘር ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ተናገሩ፡፡

የኢትዮጵያ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ለሁለት ወራት ሲያሰለጥናቸው የቆያቸውን 200 የኤ አይ ሰመር ካምፕ ሠልጣኞች በትናንትናው እለት አስመርቋል።

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ በምረቃ መርሐ ግብሩ ላይ ተገኝተው ባደረጉት ንግግር እንደገለጹት፤ አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለዛሬ ሳይሆን ለነገ መልካም ፍሬ የሚሰጥ ምርጥ ዘር ነው፡፡

የሰው ጉልበት በመቀነስ በማሽን በስፋት ማምረት እንዲቻል ቴክኖሎጂ ካልደገፈው በቀር የኢንዱስትሪዎች የማምረት አቅም ውስን ይሆናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በተለይም ከግብርናው እስከ ኢንዱስትሪው ያለው ዘርፍ በቴክኖሎጂ ታግዞ ምርታማ እንዲሆን የሚያስችል ነው ብለዋል፡፡

በዲጂታል ኢትዮጵያ ስትራቴጂ እቅዱም ቴክኖሎጂን የእድገት መሠረት አድርጎ መቅረጽ ቀዳሚው ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ፤ በሁሉም ዘርፍ ላይ የቴክኖሎጂ ድጋፍ የሚፈልግ መሆኑን ተናግረዋል፡፡

ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)፤ ኤ አይ የተፈጠረለትን ዓላማ እያሳካ ነው፡፡ የአርቲፊሻል ኢንተለጀንስ ተመራቂዎች ያገኙትን ሥልጠና በትጋት ሥራ ላይ በማዋል የኢትዮጵያን ገፅታ፣ ኢኮኖሚ



**ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)**

እንዲሁም ብልጽግና ማረጋገጥ ይቻላል፡፡ ከተመራቂዎች የሚጠበቀውም ዘላቂ ችግር የሚፈታ ፈጠራ እንድታመነጩ ነው ሲሉ አሳስበዋል።

አርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ለዲጂታል ኢትዮጵያ እድገት ወሳኝ መሆኑን አንስተው ተማሪዎቹ በሰመር ካምፕ መርሐ ግብር ከሚሰጣቸው ሥልጠና ባሻገር በሀገር አቀፍ ደረጃ የተጀመረው "የ5 ሚሊዮን ኢትዮጵያውያን ኮደርስ ኢኒሼቲቭ" ሥልጠና ቁልፍ መሠረት መሆኑንም ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

የአርቴፊሻል ኢንተለጀንስ ሠልጣኞች ዓላማቸው በፈጠራ ላይ ያተኮረ መሆን እንዳለበት የገለጹት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ታዳጊዎቹ ህልማቸውን ለመኖር መድከም እንዳለባቸውም ምክራቸውን ለግሰዋል።

አምና 30 ተማሪዎች መመረቃቸውን ያነሱት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ዘንድሮ 200 ሠልጣኞች ማስመረቅ ተችሏል፤ በቀጣይም አቅምን በማሳደግ በክረምት የሚሰጡ ሥልጠናዎች የሚቀጥሉ ይሆናል ሲሉ ገልጸዋል።

በርካታ ወላጆች የተሻለ ትምህርት ለልጆቻቸው ለማግኘት ወደ ሌላ ሀገራት ልከው በጠበቁት ልክ ልጆቻቸውን አያገኙም ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በዚህ ሰመር ካምፕ ልጆቻችው ተምረው ለዚህ በመብቃታቸው ወላጆች ደስ ሊላችሁ ይገባልም ብለዋል።

በተያያዘም ጠቅላይ ሚኒስትሩ በጽህፈት ቤታቸው ለሚገኙ ዝቅተኛ ገቢ ላላቸው ሠራተኞችና ጽህፈት ቤቱ ለሚያሳድጋቸው ህጻናት ማዕድ አጋርተዋል፡፡

ማዕድ ማጋራት የሀገር ወዳድነት ምልክት፤ የወዳጅነት ውብ ማስታወሻ ነው ሲሉ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ባስተላለፉት መልዕክት ገልጸዋል፡፡

ማዕድ ማጋራት አንጡራ ባህላችን ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ ካለን ላይ እናጋራ፤ ደስታን እንጋራ፣ እርስ በርሳችን እንደጋገፍ፤ በዓሉን ካለችን ለሌለው እያካፈልን ልባችንን እና ነፍሳችንን የሚመግቡ ትውስታዎችን በመፍጠር እናሳልፍ ሲሉ መልክታቸውን አስተላልፈዋል።

# የኢትዮጵያዊነት...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በሚያደርጋቸው ኢትዮጵያዊነት ስሜት ከያሉበት ተጠራርተው በጋራ መሰለፋቸው ለድሉ ትልቅ አስተዋጽኦ ማድረጉን ታሪክ አይዘነጋውም።

ይህ የአንድነት ስሜት ትናንት ተብሎ ከሚወራ ታሪክ ባለፈም ለዛሬው ትውልድ ስንቅ ሆኖ በጎሳ፣ በቋንቋና በኃይማኖት ሳይከፋፈሉ ሀገርን ከፍ በሚያደርጉ ሀገራዊ ፕሮጀክቶች ላይ ዜጎች በጋራ እንዲሰለፉ አቅም ይፈጥራል።

የኢትዮጵያውያን ሕብር ትናንት ለነበረው ድል ፣ ለዛሬ ጥንካሬ እንዲሁም ለነገ ተስፋ ያለው አበርክቶው እንዴት ይገለጻል፤ በሚሉ ጉዳዮች ላይ የታሪክ ባለሙያዎችና አባት አርበኞች ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

የጥንታዊት ኢትዮጵያ ጀግኖች አርበኞች ማኅበር ፕሬዚዳንት ልጅ ዳንኤል ጆቴ መስፍን እንደሚሉት፤ ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች መገኛ ብትሆንም ሕዝቡ በጋራ ባህል ፣ታሪክ እንዲሁም ወግና ሥርዓት የተሳሰረ ነው፡፡

የኢትዮጵያውያን ኅብር በቀላሉ ሊበጠስ የማይችል በመሆኑ በዓድዋና በካራማራ ጦርነት ወቅት ሀገርን ከውጭ ወራሪ ጠብቋል ያሉት ፕሬዚዳንቱ፤ በዓድዋ ጦርነት ጊዜ የተሰለፈው ሕዝብ ከተለያዩ አካባቢዎች የመጣና ተመሳሳይ ቋንቋ የማይናገር ቢሆንም ሁሉም ግን ለሀገሩ በአንድ መንፈስ በጋራ መሰለፍ መቻሉን ይናገራሉ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ለሕይወቱ ሳይሰስት አንድ ሺ 80 ኪሎ ሜትር በእግሩ ተጉዞ ለመዋጋት የወጣው ልዩነቱን ጥሎ የጋራ ሀገሩን ለመጠበቅ ነው። አርበኛው ሲነሳ መንግሥት ለእያንዳንዱ ልብስና ጫማ፣ መዋጊያ መሣሪያ እንዲሁም ደሞዝ አልሰጠውም። ይልቁንም የራሱን ንብረት ይዞ፤ ብሞትም ለሀገሬ ነው ብሎ ድል ያደረገው የኢትዮጵያዊነት ኅብር ስለነበረው ነው ይላሉ።

ልጅ ዳንኤል ጆቴ፤ በሀገሪቱ በተለያዩ ጊዜያት ወደሥልጣን የመጡ መንግሥታት የተለያዩ ፖለቲካ ርዕዮተ ዓለም ሲተገበሩ የጋራ የሆኑ እሴቶችና ታሪኮች እንዲደበዝዙ ቢደረግም እንኳን የአሁኑ ትልውልድ ኢትዮጵያ የበርካታ ማንነቶች ባለቤት መሆኗ ውበት መሆኑን የተረዳና የአንድነት ስሜትን የተገነዘበ መሆኑን ያስረዳሉ። ሀገሪቱን ሊበጠብጡ የሚፈልጉ አካላት ሃሳባቸው እንዳይሳካ ያደረገው ይኸው የአንድነት ስሜት መሆኑንም ይገልጻሉ፡፡

የዛሬው ትውልድ ጠያቂ እንደመሆኑ ለሀገሩ የሚጠቅም ጉዳይ ሲኖር ምን ተፈጠረ ብሎ ያነሳል፤ ምሁራኑም ኅብርን የሚፈትኑ ጉዳዮች ሲነሱ በወቅቱ መፍትሄ ሊያበጁ ይገባል ሲሉ አስተያየታቸውን ሰጥተዋል።

በተለይ የተለያዩ ብሔር ብሔረሰቦች ውስጥም ችግሮች ሲነሱ ሰላምን ሊያሰፍኑ የሚችሉ አስፈላጊ ሕግና አሠራሮች በመኖራቸው እነሱን አጥንቶ ማዳበርና መተግበር እንደሚገባም ይጠቁማሉ።

በ2016 ዓ.ም በአዲስ አበባ የተገነባው የዓድዋ ሙዚየም የአሁኑ ትውልድ የጋራ ታሪክ ነጸብራቅ ነው ያሉት ልጅ ዳንኤል ጆቴ፤ በአዲሱ ዓመት ይህንን የመሰሉ አንድነትን የሚያጠናክሩ ሥራዎች መሥራት ከተቻለ ለመጪው ትውልድ የአብሮነት መሠረት ማስቀመጥ እንደሚቻል ያነሳሉ።

የታሪክ ተመራማሪና የሀገር ሽማግሌ የሆኑት አህመድ ዘካርያ (ፕ/ር) በበኩላቸው ኢትዮጵያ ያገኘቻቸው ድሎች ሁሉ መሠረታቸው ህብረት ነው ይላሉ፡፡

ቀደምት አባቶች በአብሮነታቸው ደማቅ ታሪክን ጽፈው ማለፋቸውን ጠቁመው፤ የአሁኑ ትውልድ ደግሞ ልዩነቱን ወደ ጎን በመተው የዓባይ ግድብን ለመገንባት በጋራ በመቆም የራሱን ታሪክ መጻፉን ያስታውሳሉ። ከግድቡ በተጨማሪ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ-ግብሮች ሌላኛው የአሁኑ ትውል የአብሮነት ማሳያዎች መሆናቸውን ይጠቁማሉ።

ኅብር ለትናንት ድል ፤ ለዛሬ ጥንካሬ እንደሆነ ሁሉ ለነገው ትውልድም ቀጣይነት ያለው ሥራ አስፈላጊ መሆኑን ተናግረው፤ አንድነትን ለማጠናከር የውስጥ ችግሮችን ተወያይቶ መፍታትና ችግሮችን በሰላማዊ መንገድ ማረቅብ ይገባል ሲሉ ሃሳባቸውን ሰጥተዋል።

ህብረ ብሔራዊነትን ሊያጠናክሩ የሚችሉ ሀገራዊ ጉዳዮችን ማከናወን፣ የጋራ ጠላቶችን በአንድነት ስሜት መመከትና ሰላምን መፍጠር የምንጊዜም የትውልዱ ዋና አጀንዳዎች ሊሆኑ እንደሚገባም ልጅ ዳንኤል ጆቴ እና አሕመድ ዘካሪያ (ፕ/ር) ተናግረዋል።

# ድህነትን ለመሻር...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

በክብርም በቁጥርም ትልቅ የሆነው፤ ሰፊና ሰጪ ምድርን የታደለው ሕዝቧ፣ ሀገሩ ከእጦትና ከችግር የተላቀቀች፣ በኢኮኖሚ አቅሟም የበለጸገች ውብና ለኑሮ ምቹ ሀገር ሆና ማየትን ይሻል፡፡ መሻት በጥረት እንጂ በተስፋ ብቻ እውን አይሆንምና፣ ነገ ላይ የበለጸገችውን ኢትዮጵያ ማየት ይቻለን ዘንድ መንግሥትና ሕዝብ ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወኑ ይገኛሉ፡፡

ለመሆኑ ዛሬ ላይ ያሉ ሰፋፊ የልማት ሥራዎች፣ የፖለቲካ መረጋጋትን ለማስፈን የሚደረጉ ጥረቶች ነገ ልናያት የምንሻትን የበለጸገች ኢትዮጵያ እውን ያደርጉልን ይሆን? የነገዋን ብሩህ ኢትዮጵያ ማየት ይቻለን ዘንድ ከእያንዳንዱ ዜጋስ ምን ይጠበቃል?

የፖለቲካ ምሁሩ ዶ/ር ሙሉጌታ ደበበ የአንድ ሀገር ነገ የሚመሠረተው በትናንት ታሪኩና ዛሬ ላይ በሚሠራ ሥራ ነው ይላሉ፡፡ በሀገራችን ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ለውጦችን ለማምጣት በርካታ ሥራዎች ሲሠሩ መቆየታቸውንም ያወሳሉ፡፡ በለውጡ መንግሥት ደግሞ እንደ ሀገር ግባችንን "ብልጽግና" አድርገን ዘርፈ ብዙ ተግባራትን እያከናወንን እንገኛለን ያሉት ምሁሩ፣ የጀመርነው ጉዞ ወደ በለጸገች ኢትዮጵያ የምንሸጋገርበት ጊዜ ላይ ለመሆናችን ማሳያ ነው በማለት አስተያየታቸውን ይሰጣሉ፡፡

የፖሊሲና የሕዝብ አስተዳደር ምሁሩ ዶ/ር ገመቹ አራርሳ በበኩላቸው፣ በሀገራችን ካለፉት 5 እና 6 ዓመታት ወዲህ "ሁለንተናዊ ብልጽግናን ማምጣት" የሚል ግልጽ የሆነ አቅጣጫ ተቀምጦ ዘርፈ ብዙ ተግባራት እየተከናወኑ መሆናቸውን ያነሳሉ፡፡ በቀደሙት ሥርዓተ መንግሥታት የተከናወኑ መልካም ተግባራትን እንደ ሀብት በመውሰድ፣ ቀድሞ በነበረን ጉዞ የሀገራችን እድገት ብዙ ርቀት መጓዝ የተሳነው ለምንድነው የሚለው ጥያቄ በጥናት የተደገፈ ምላሽ እንዲያገኝ በማድረግ፣ ግኝቶችን መነሻ ያደረጉ ፖሊሲና ስትራቴጂዎች ተነድፈው እየተሠራባቸው እንደሚገኙም ይናገራሉ፡፡

እንደ ዶ/ር ገመቹ ማብራሪያ፣ ተጨባጭ ኢኮኖሚዊ ለውጥን ለማምጣት ከዚህ ቀደም ሲሠራበት የነበረውን የኢኮኖሚ አቅጣጫ መቀየር አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ሀገራችን ያላትን እምቅ አቅም ባገናዘበ መልኩ "ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ፖሊሲ"ን በመንደፍ ወደ ሥራ መግባት ተችሏል፡፡ በዚህም በርካታ ለውጦች ተመዝግበዋል፡፡

ከዚህ ቀደም የነበረው ግብርና መር ኢንዱስትሪ የኢኮኖሚ አቅጣጫ ግብርናው ላይ ብቻ የተመረኮዘ መሆኑ የታሰበውን ያህል ለውጥ ማስመዝገብ፣ የኢኮኖሚ ሽግግርንም ማምጣት አልተቻለውም ነበር፡፡ ስለሆነም ይህን የኢኮኖሚ አቅጣጫ ወደ ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ አቅጣጫ መቀየሩ አስፈላጊነቱ ታምኖበት በተወሰደው ርምጃ ግብርናውን በተሻለ ትኩረትና ጥንካሬ በመያዝ ምርትና ምርታማነት እንዲጨምር ማድረግን ጨምሮ ከዚህ ቀደም ትኩረት ያልተሰጣቸው እንደ ማዕድንና ቱሪዝም ያሉ በርካታ ዘርፎች ትኩረት ማግኘት ችለዋል፡፡ በዚህም በርካታ ከውጪ የሚገቡ ምርቶችን በሀገር ውስጥ ምርቶች በመተካት፣ ወደ ውጪ የሚላኩ ምርቶችንም በማበረታታትና በብዛትና በጥራት በማሳደግ ተጨባጭ ለውጦችን ማምጣት ተችሏል፡፡

እየተተገበረ ያለው የኢኮኖሚ አቅጣጫ ከጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት አንስቶ የውጪ ኢንቨስተሮችን አሳታፊ በሆነ መልኩ መመራቱ ከዚህ ቀደም ሀብት በጥቂቶች እጅ ብቻ እንዲሆን ሲያደርግ የነበረውን የኢኮኖሚ አካሄድ መቀየር የቻለ ነው ያሉት ዶክተር ገመቹ፤ እየተከተልን ያለነው አካታችና ዘርፈ ብዙ የኢኮኖሚ አቅጣጫ በጣም ትልቅ ለውጥ እያመጣ ስለመሆኑ በየዘርፉ እየመጡ ያሉ ለውጦች ጉልህ ማሳያ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡

በቅርቡ በተተገበረው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የውጪ ምንዛሪ ምጣኔው በገበያ ዋጋ መወሰኑ አሁን ላይ ይህን ለውጥ አምጥቷል ለማለት ባይቻልም፣ በሂደት ግን በተለይ በውጪ ምንዛሪ እጦትና እጥረት ሳቢያ የተሳሰሩ ዘርፎች የሚፈልጉትን ውጪ ምንዛሪ እንዲያገኙ እድል የሚሰጥ በመሆኑ በሂደት ለውጥ የሚያመጣ መሆኑ እሙን ነው ብለዋል፡፡

በሀገራችን ለሁሉም ዘርፍ የተሠሩና እየተሠሩ ያሉ የልማት ሥራዎች በሀገራችን ሁለንተናዊ ብልጽግናን ለማምጣት ብሩህ ተስፋን እንድንሰንቅ የሚያደርጉ ናቸው ያሉት ዶክተር ገመቹ ብልጽግናችን እውን የሚሆነው በሕዝብ ጥረት ነው ይላሉ፡፡ ሀገር ብትለወጥና ብታድግ ተጠቃሚው ሕዝብ፣ ፍሬውን የሚበላው የነገው ትውልድ ነው ያሉት ምሁሩ ይህን እውን ለማድረግ እንደ ሕዝብ የሥራና የጊዜ አጠቃቀም ባህላችንን መቀየር፣ ትኩረታችንን ልማት ላይ ማድረግ፣ እውቀትን ለበጎ ተግባር ማዋል ይጠበቃል የሚል አስተያየት ሰጥተዋል፡፡

የፖለቲካ ምሁሩ ዶክተር ሙሉጌታ በበኩላቸው፣ አልመን የተነሳንበትን ብልጽግና እውን ለማድረግ የሀገር ሰላም ወሳኝ ቅድመ ሁኔታ መሆኑ ላይ ያሰምራሉ፡፡

የተበላሹ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ግንኑነትን ለማስተካከል በተለያየ መልኩ የሚደረጉ ጥረቶችና የሀገር አንድነትን ለማጽናት በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አማካኝነት እየተከናወኑ ያሉ ተግባራት ነባር ጣጣዎቻችንን ቋጭተን ወደ አዲስ ምዕራፍ ልንሻገር ጉዞ መጀመራችንን አመላካች ናቸው ያሉት የፖለቲካ ምሁሩ፣ በልማትም ሆነ በፖለቲካው ዘርፍ እየተደረጉ የብልጽግና ጎዳናን የማቅናት ጥረቶች ተስፋ ሰጪ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡ ጥረቶቹ እንዲሳኩ ሁሉም የበኩሉን ከተወጣ፣ መወያየትን መርጠን በጠረጴዛ ዙሪያ ከተቀመጥን የልማት ሥራዎቻችን የበለጠ ፍሬያማ፣ የበለጸገችዋን ኢትዮጵያ እውን ማድረግም ሩቅ አይሆንም በማለት አስተያየታቸውን ቋጭተዋል፡፡

# የብልጽግና...

**ከ1ኛው ገጽ የዞረ**

ህብረተሰብ ሁኖ መዝለቅ አለበት ሲል አብራርቷል፡፡

እንዲሁም ዛሬን ተምሮ እራሱን ለመቀየር የሚተጋ ወጣት በመሆን በተሠማራበት ሙያ ከእኔነት ወደ እኛነት በመምጣት በጋራ ለጋራ ሰላም ሃላፊነት መውሰድ እንደሚገባ ጠቁሟል፡፡

በዚህም አያቶቹ ያስረከቡትን ሀገርን በማስቀጠል ሂደት ውስጥ ከነማንነቷ ከፍታዋንና የአፍሪካ መመኪያነቷን የማስቀጠል እንዲሁም ለነገዋ የተሻለች ኢትዮጵያ ሃላፊነት ያለበት መሆኑን ይገልጻል፡፡

ጥቂት የሚባሉ ወጣቶች ትክክለኛ ባልሆነ መንገድ ሲሳተፉ የሚታይ መሆኑን ወጣት ይሁኔ ጠቅሶ፤ አብዛኞቹ ወጣቶች ስፖርትን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች የሀገራቸውን ባንዲራ ከፍ አድርገው እያውለበለቡ እና ስሟን እያስጠሩ መሆኑን ተናግሯል።

በመሆኑም ወጣቱ ትውልድ ሀገሪቱ በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ብትሆንም በሰላማዊ መንገድ በመግባባትና በመስማማት ችግሮችን የሚቀርፍ ፣ለነገ የሚጠቅሙትን ለቀጣይ ትውልድ የሚያስተላልፍና ለሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ እድገትና ብልጽግና በየዘርፉ ሃላፊነቱን መወጣት እንዳለበት መልእክቱን አስተላልፏል።

የአስካል በጎ አድራጎት ማህበር መሥራችና ሥራ አስኪያጅ አቶ በላይ ንጉሤ በበኩሉ፤ ወጣት ማለት "የሀገር አንጓ" ማለት ነው ሲል ይገልጸዋል፡፡

ይህም ማለት ያለፈውና የሚመጣው ትውልድ ማዕከል በመሆን ትናንት ከአባቶቹ የተረከበውን ሀገር እና ታሪክ ለቀጣዩ ትውልድ የሚያስቀጥል የታሪክ አንጓ ነው ብሏል፡፡

"የባለራዕይ ወጣት ነገ የሚጀምረው ከዛሬ ነው፤ ዛሬን ያልሠራ ሰው ነገን ማሰብ አይችልም" ያለው አቶ በላይ፤ ነገአቸው እንዲያምር ወጣቶች ከነገ አንጻር ዛሬን በትክክል በመኖር የሚያፈልግ መሆኑን ይገልጻል ፡፡

በዚህም የወጣቱ ዛሬነት ምን ይመስላል እንዲሁም ነገ ሲታሰብ ዛሬን መነሻ በማድረግ ተስፋ ይታያል ወይ የሚለውን ማየት ያስፈልጋል ብሏል፡፡

እንዲሁም የሚኖሩለትን ዓላማ ከማወቅ ጀምሮ ሀገር ምን ይጎልበታል፣ ከኔ ምን ይጠበቃል በሚለው ዙሪያ በየተሠማሩበት ዘርፍ ከውስጣቸው ፍላጎት ባሻገር ሀገር የሚጎልባት ብዙ ያልተሠሩ ሥራዎችን ለማሟላት የበኩላቸውን ሚና መወጣት እንዳለባቸው ይገልጻል፡፡

በመሆኑም በሥነምግባርና በመልካም ሥብዕና በመታነጽ ለሀገር እድገትና ሰላም የሚጠበቅበትን ሚና በመወጣት ለነገ ተረካቢዎች የሚያኮራ ሥራና ታሪክ ማስተላለፍ አለባቸው ሲል ተናግሯል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## የዛሬ ትጋታችን ለብሩህ ነገዎቻችን መሠረት የሚጥል ነው

የየትኛውም ሀገር እጣ ፈንታ የሚወሰነው በዜጎች ማህበረሰባዊ ማንነት ነው። ይህ ማንነት ዜጎች በዘመናት ካካበቷቸው ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ እሴቶች የሚገነባ ፤ በየዘመኑ በሚፈጠሩ የለውጥ እሳቤዎች እየታደሰ እና እያደገ ዘመኑን በሚሸከም ሁለንተናዊ አቅም እየጎለበተ የሚሄድ ነው።

ይህ ማህበረሰባዊ ማንነታቸው አሁን ላሉበት እድገትም ሆነ ውድቀት፤ በታሪክ ሂደት ውስጥ ለነበራቸው የትርክት ከፍታም ሆነ ዝቅታ፤ ከዛም ባለፈ ነገዎቻቸው ምን ሊመስሉ እንደሚችሉ ተናጋሪ ልሳን ነው። በብዙ መልኩ እንደ ሀገር ሊኖራቸው የሚችለውን መልክ በትክክል ማሳየት የሚችል መስታወትም ነው።

ዘመኑን በሚዋጅ የአስተሳሰብ መሠረት ላይ የተገነባ ማህበረሰብ ዛሬን ጨምሮ ነገዎቹ ብሩህ ስለመሆናቸው፤ የተገነባበት የአስተሳሰብ መሠረት በራሱ ማስተማመኛ ነው። በተቃራኒው በትናንት አስተሳሰብ ዛሬ ላይ ቆሞ ነገን የሚጠብቅ ማህበረሰብ ዛሬን ጨምሮ ነገዎቹ በትናንት ጥላ ውስጥ ማደራቸው የማይቀር ነው።

በትናንት ጥላ ውስጥ መገኘት ፍጥረታዊ ከሆነው የለውጥ /የመለወጥ/ ሂደት ውጪ የሚያደርግ፤ ትናንቶችን ደጋግሞ ወደመኖር የሚያመጣ ፤ ከሠብዓዊ መሻት ጋር በተቃርኖ መቆምን የሚያስከትል ነው። ይህ ደግሞ ከዘመን ጋር አብሮ ካለመጓዝ ጋር በተያያዘ ሊፈጠር ለሚችል ማህበራዊ ቀውስ የሚዳርግ ነው።

በትናንት ጥላ ውስጥ የመኖር ችግር የድህነት እና የኋላቀርነት ዋነኛ ምክንያት ከመሆን ባለፈ፤ ትናንቶች ከሚፈጥሩት መለመድ ጋር በተያያዘ ፤ማህበረሰባዊ ድንዛዜን ያመጣል፤ነገን በተሻለ ተስፋ አስቦ መንቀሳቀስ የሚያስችል ማህበረሰባዊ መነቃቃትን ያሳጣል። ድህነትን እና ኋላቀርነት እጣ ፈንታ አድርጎ በመቀበል የጠባቂነት መንፈስን ያበረታታል።

እኛ ኢትዮጵያውያን ከትናንቶች ጋር በነበረን ጠንካራ ቁርኝት በብዙ መንገድ ዛሬዎቻቸውን ካጡ፤ ነገዎቻቸው ካባከኑ ሕዝቦች ጎራ የምንሰለፍ ነን። ከትናንት መማር ባለመቻላችን በተመሳሳይ ትናንቶች ውስጥ ብዙ ዋጋ እየከፈልን ኖረናል። በዚህም ድህነት እና ኋላቀርነት እጣ ፈንታችን ሆነው ዘመናት አልፈዋል።

በአንድ የታሪክ ምእራፍ ዓለምን ያስደመመ፤ ከታላላቆቹ ጎራ ያሰለፈ፤ ከዘመኑ በቀደመ አስተሳሰብ የተገራ ማህበረሰብ እንዳልነበርን፤ የተቃርኖ አስተሳሰቦችን አቻችሎ መሄድ የሚያስችል ማህበራዊ ስክነት አጥተን፤ የተሻሉ ትናንቶቻችንን አጥፍተን፤ ነገዎቻችንን ባጠቆሩ ዛሬዎች ውስጥ ለመኖር ተገደናል።

ለየዘመኑ አስተሳሰቦች ባይተዋር ሆነን፤ በብዙ ማህበረሰባዊ ድባቴ ውስጥ በብዙ ቁዘማ አልፈናል። መሆን በምንፈልገው እና እየሆንን ባለው እውነታ መካከል የተፈጠሩ ልዩነቶችን ማስታረቅ የሚያስችል ማህበረሰባዊ የእውቀት መነቃቃት /ተሃድሶ/ አጥተን በድንግዝግዝ ዛሬን ብቻ አሸንፎ በመውጣት የሕይወት መርህ ዘመናትን አስቆጥረናል።

ዛሬ ግን ከዚህ ሁሉ የዘመናት የትናንቶች የጥላ ትርክት ወጥተን፤ ዛሬ ላይ ብሩህ የሆኑ ነገዎቻችንን አይተን፣ መሥራት በምንችልበት አዲስ የታሪክ ምዕራፍ ላይ እንገኛለን፡፡ የራሳችንን እጣ ፈንታ ብሩህ አድርጎ በሚያይ ማህበረሰባዊ የእውቀት መነቃቃት /ተሃድሶ ውስጥ ነን። ትናንቶችን ለትናንት ጥለን ዛሬዎቻችንን ነገን ብሩህ በሚያደርጉና ዘመኑን በሚዋጁ የለውጥ እሳቤዎች እያነጽን ነው።

ከለውጥ ማግስት ጀምሮ በቁጭት «ድህነት እጣፈንታችን አይደለም፤ ትልቅ ነበርን ትልቅ እንሆናለን፣ ከትናንት እንማራለን እንጂ በትናንት አንኖርም፣ ድህነትን ታሪክ እናደርጋለን...» እያልን ከፍ ባለ ድምጽ የምናሰማቸው ከለውጥ መንቃታችን የተወለዱ አሻጋሪ እሳቤዎቻችን የዚህ እውነት ተጨባጭ ማሳያዎች ናቸው።

በእነሱ ላይ ቆመን የጀመርነው አዲስ የታሪክ ምእራፍ ግንባታ ብዙ ዋጋ ቢያስከፍለንም፤ ከፍ ያለ ትጋት እና ቁርጠኝነት ቢጠይቀንም፤ የለውጥ መነቃቃቱና መነቃቃቱ የፈጠረው የአስተሳሰብ ተሀድሶ፤ ብዙ ትውልዶችን ታሳቢ የሚያደርግ፤ ለብሩህ ነገዎች መሠረት የሚጥል እና የሚያጸና ነው። ከዚያም በላይ አዲስ ተራማጅ ማህበረሰባዊ ማንነት መገንባት የሚያስችለን ነው።

አዲስ ተራማጅ ማህበረሰባዊ ማንነታችን ከትናንት አንገት አስደፊ ታሪኮቻችን የሚታደገን፤ ለቀደሙ ደማቅ ታሪኮቻችን ተጨማሪ ድምቀት የሚያላብስ፤ የከሰርንባቸውን ብዙ ዘመናት በይቻላል መንፈስ በብዙ መካስ የሚያስችል የፍጻሜ ጅማሬ ነው።


## አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ዛሬን ለነገ ትሩፋት

ቴልጌልቴልፌልሶር (የኩሽ አሽክታብ)

መጪውን በኳለና በሳለ መልኩ ‹የዛሬ ትጋት ለነገ ትሩፋት› በሚል አመርቂ ሃሳብ የአዲስ ዓመት የመጨረሻ እለት የሆነውን ጳጉሜን አምስትን ዋጅተናል፡፡ እንደሚታወቀው ጳጉሜን ወር የአስራ ሶስት ወር ጸጋን የያዘ የዘመን አጭር ግን ደግሞ የታሪክ ሀብታም ወር ነው፡፡ በዚህ የአሮጌው ዓመት ማብቂያ ላይ አዲሱን ዓመት በበጎ ሃሳብና ተስፋ እንድንቀበለው በሚያደርግ የመንፈስ ንቃት ላይ እንገኛለን፡፡

ኢትዮጵያ ሀገራችን በአሁኑ ሰዓት በሃሳብ የበለጸገ፣ ለሃሳብ ቅድሚያ የሚሰጥ ሃሳባውያን ያስፈልጓታል፡፡ ሃሳብና ሃሳባውያን የሚፈጠሩት ደግሞ ዓላማ ባለው፣ ለአንድ ግብ በቆመ ብሄራዊ ጥቅም በኩል ነው፡፡ አምስቱም የጳጉሜን ቀናት ስያሜዎች ሀገር ከምትፈልገው፣ ሕዝብ ከሚሻው፣ የትውልዱ ጥያቄ ከሆነ እውነታ በኩል የመነጩ ናቸው፡፡

> **ነገ የተስፋ ቀን ነው፡፡ የነገ ቀን ብዙዎች ህልማችንን ያስቀመጥንበት ካዝና ነው። እንደሀገር እንደግለሰብ በሆነልን የምንለው ነገ ውስጥ ያለ ነው። ይሄ ቀን ደግሞ በዛሬ ትጋት፣ በዛሬ ምክክር፣ በአሁን እርቅና ሰላም የሚዳብር ነው**

ነገ የተስፋ ቀን ነው፡፡ የነገ ቀን ብዙዎች ህልማችንን ያስቀመጥንበት ካዝና ነው፡፡ እንደሀገር እንደግለሰብ በሆነልን የምንለው ነገ ውስጥ ያለ ነው፡፡ ይሄ ቀን ደግሞ በዛሬ ትጋት፣ በዛሬ ምክክር፣ በአሁን እርቅና ሰላም የሚዳብር ነው፡፡ በወንድማማችነት፣ በትብብር፣ በድግግፍ የሚጸና ነው፡፡ የዛሬ ትጋት ለነገ ተስፋ ብለን በመሪ ሃሳብ ስንነሳ ለነገ ህልሞቻችን የዛሬን ሃላፊነት መሠረት በማድረግ ነው፡፡

በርካታ የሳይንስ ጥናቶች፣ እልፍ የሥነ ልቦና ምርምሮች ካለፈው ይልቅ የሚመጣው እንደሚልቅ የሚናገሩ ናቸው፡፡ ልክ እንደዚህ ሁሉ ባለፈው ጣጣው ዛሬውን የሚኮንን ለመጪው የሚሆን ትሩፋት እንደሌለም ይናገራሉ፡፡ መጪው ካለፈው የሚልቅ ከሆነ እንደተስፈኛ ሀገር ልናደርግ የሚገባው ሶስት ወሳኝ ነገር አሉ ብዬ አምናለሁ .. ይቅርታ ፍቅርና ተስፋ ናቸው፡፡

ይቅርታ ትናትን፣ ፍቅር ዛሬን፣ ተስፋ ደግሞ ነገን እንድንኖር የሚያደርጉን የሕይወት ዋስትናዎቻችን ናቸው፡፡ ትናንት በብዙ ጣጣው ወደዛሬ መጥቶ ዛሬን አበላሽቶብናል፡፡ ዛሬ በትናንት ጣጣው ወደነገ እንዳይሄድ በቃ ብለን ዛሬ ላይ የምናቆመው ከላይ በገለጽኩት ሶስት መንገድ ነው፡፡ ይቅርታ ፍቅርና ተስፋ ከአሮጌ አስተሳሰብ ወጥተን ወደከፍታ የምንሸጋገርባቸው መንገዶቻችን ናቸው፡፡

አዲስነት ይቅርታ ፍቅርና ተስፋን የቀየጠ ሰውነትን ነው ፡፡ በአዲሱ ዓመት ወደ ከፍታና ወደላቀ ሀገራዊ በረከት ለመሄድ እኚህ ሶስት እውነቶች ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊዎቻችን ናቸው፡፡ አብዛኛውን ጊዜ ስናስብና እንደሀገር እቅድ ስናወጣ እነዚህን ነገሮች ግንዛቤ ውስጥ ባለማስገባት ነው፡፡

አዲስ ዓመት ባልነጻ ልብና ባልተቀደሰ አእምሮ ቢመጣ ትርጉም የለውም፡፡ ከምንም በፊት አእምሮና ልባችንን ለሰውነት ማስገዛት ይኖርብናል፡፡ በርካታ አዲስ ዓመታትን እንዲሆንልን በምንመኘው በጎ ምኞት ተቀብለን እናውቃለን አንዳቸውም ግን ትርጉም ያለው ነገር ሳይሰጡን አልፈዋል፡፡ ምክንያቱ ደግሞ ለምኞታችን የሚሆን ፍቅር ወላድ፣ አብሮነት ጻናሽ እውነት ስለሌለን ነው፡፡ ዛሬ ላይ እያደረግናቸው ያሉ ነገሮች ወደነገ ሄደው ሕይወታችን የሚሆኑ ናቸው፡፡ ሰላም ከሆነ የምንፈልገው ስለሰላም ዋጋ እንክፈል፡፡ አንድነት ከሆነ ስለኢትዮጵያዊነት እናውጋ፡፡

አዲሱ ዓመት በበጎ ሃሳብ የፍቅርን ዘር የምንዘራበት፣ የጥላቻና የጦርነትን አሜኬላ የምንነቅልበት ነው፡፡ የፍቅር ዘር አብሮነትን የሚሰጠን ወደምንፈልገው ወደየትኛውም አቅጣጫ በድል የምንሄድበት ነው፡፡ ሊነቀሉ የሚገቡ በጥላቻ የዘራናቸው ብዙ የጉስቁልና ዘሮች አሉ፡፡ ፍሬ መስጠት ሲገባቸው እንክርዳድ እያሳጨዱን ከክብር ሥፍራ አጉለውናል፡፡ እነዚህ አራሙቻዎች በአዲሱ ዓመት ተወግደው በሁሉን አቃፊ የጋራ ወግ መተካት አለባቸው፡፡

የዛሬ ትጋቶቻችን የነገ ትሩፋቶቻችን ናቸው። ትሩፋት በረከት፣ ጸጋ ማለት ነው፡፡ መትረፍረፍ የሚለው የጸጋ ስምም በዚህ ስያሜ የሚጠራ ነው። የዛሬ ትጋት ለነገ ትሩፋት የሚለው መነሻ ሃሳብ እድልና ድልን በአንድ ያስተሳሰረ፣ ከድህነት ወደ እድገት፣ ከጦርነት ወደ ሰላም የሚወስድ የጸጋ መነሻ ነው፡፡ ትሩፋት በትጋት የሚመጣ የላብ ውጤት ነው፡፡ ነገን የትሩፋት ጊዜ ለማድረግ ዛሬን መትጋትና መበርታት ያስፈልጋል፡፡

ነገን ዛሬ መሥራት የሚል የቆየና በእያንዳንዳችን ልብ ውስጥ የተሳለ ሀገረኛ አባባል አለው፡፡ የጳጉሜን 5 መሪ ቃል አንድምታም እንዲሁ ነው። ልብ ብለን ከሆነ ዛሬ ላይ ዋጋ እየከፈልንባቸው ያሉ የፖለቲካ፣ የማንነት፣ የሰላም፣ የደህንነት መሰል ጥያቄዎች ትናንት ላይ ያልተሰራባቸው በእንዲሁ የታለፉ ናቸው፡፡ የዛሬ ትጋት የነገ ትሩፋት ግን ከስህተቶቻችን ተምረን ያለፈውን በይቅርታ ያለውን በእርቅ መጪውን ደግሞ በፍቅርና በአብሮነት እንድንቀበለው የሚያደርግ የተሀድሶ ሃሳብ ነው፡፡

ያለመጠራጠር ተሀድሶ ያስፈልገናል፡፡ ፖለቲካው፣ ፖለቲከኛው፣ አክቲቪስቱ ሁላችንም የለውጥና የስክነት ተሀድሶ ያስፈልገናል፡፡ ተሀድሶ ብዙ ትርጉም ቢኖረው አሁን ባለው የሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ግን አክሳሪ እና አዋራጅ ከሆነ የክሽፈት ልምምድ ወጥተን አዋጪና አትራፊ ወደሆነ አዲስ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ልምምድ መሻገር የሚለውን ትርጓሜ ይይዛል፡፡ ኢትዮጵያ ሀገራችን ሰላሟን በምክክር፣ ልማቷን በትብብር፣ አንድነቷን በኢትዮጵያዊነት ለመጽናት እንቅስቃሴ ላይ ትገኛለች፡፡ ይሄ ተስፋዋ በአዲሱ ዓመት እንዲጎመራ የጋራ ምኞት አለን፡፡

ትርፍ ያለው ለሀገር እሴት የሚጨምር አስተሳሰብ ከፖለቲካው ወደፖለቲከኞቻችን ከዛም ወደማህበረሰቡና ትውልዱ እንዲሰርጽ ያረጁና ያፈጁ ጦርነት ወላድ አስተሳሰቦች መሻር አለባቸው፡፡ ለዚህ ደግሞ የጋራ ትርክት፣ የአብሮነት ወግ አጅግ ጠቃሚ ነው፡፡ ለዚህ መሸጋገሪያ የሚሆነን ደግሞ ከአሮጌው ዓመት ጋር አሮጌ አስተሳሰባችንን ጥለን ከአዲሱ ዓመት ጋር በአዲስ አእምሮና ልብ ነገን የምንሠራበትን የሀሳብ መዋጮ ማዋጣት ነው፡፡

ፖለቲካ እና ልዩ ልዩ

# ነፃ ሃሳብ

## የዛሬ ትጋታችን የነገ ትሩፋታችን ነው

**አሲሴሮ**

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በጥንታዊነታቸው ከሚታወቁ ጥቂት ሀገሮች አንዷ ነች፡፡ ይህም ጥንታዊነቷ የሰው ልጅ መገኛ እንድትሆን አድርጓታል፡፡ ከዚህም ባሻገር የራሷ የሆነ ፊደል እና የዘመን አቆጣጠር ባለቤት እንድትሆን አስችሏታል፡፡ ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ የግብርና ስራን ከጀመሩ ጥቂት ሀገራትም አንዷ እንደሆነች መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ የታሪክ ድርሳናት እንደሚያትቱትም ኢትዮጵያ በአባይ ወንዝና እና በቀይ ባሕር አማካኝ ስፍራ ላይ የምትገኝ ሀገር በመሆኗ የአካባቢው አውራ ሆና ለዘመናት ኖራለች፡፡

የሀገሪቱን እድገት የማይሹ አካላት ለዘመናት በሰሩት ደባ ኢትዮጵያ በቀይ ባሕርና አካባቢ የነበራት ሚና እያሽቆለቆለ መጥቶ የኢሕአዴግ ዘመን እስኪያበቃ ድረስ ተሰሚነቷ እና ተጽዕኖ ፈጣሪነቷ እንዲያሽቆለቁል አድርጓል፡፡ ይህም ሀገራዊ ቁጭት ሲፈጥር ቆይቷል፡፡ የኢሕአዴግን መውደቅ ተከትሎ በተፈጠረው ሀገራዊ መነሳሳት እና የመንግስት ለውጥ ሀገሪቷ በአዲስ መነቃቃት ውስጥ ጥገኛለች፡፡ ኢትዮጵያ እና ኢትዮጵያዊነት ዳግም እያበቡ ነው፡፡ በሁሉም መስክ የኢትዮጵያን ገናናነት የሚመልሱ አስተሳሰቦች እና ተግባራት መድረክ እየተቆጣጠሩ ነው። በተለይም ለጋሽ እንጂ ተመጽዋች አትሆንም የሚለው አስተሳሰብ እየጎለበተ ከመጣ ውሎ አድሯል፡፡

ኢትዮጵያ ለዘመናት ያህል ነጻነቷን ጠብቃ የኖረች የጥቁር ሕዝቦች ተምሳሌት ብትሆንም በምግብ ሰብል እራሷን ባለመቻሏ ነጻነቷን በሚገባ ሳታጣጥም ኖራለች፡፡ በአድዋ የተገኘው ድል በቅኝ ገዢዎች የፈረጠመ ኢኮኖሚ ሲጠመዘዝ ኖሯል፡ ፡ የኢትዮጵያ ኩራትና ድል በስንዴ ልመና ኮስሶ በዓለም መድረኮች ሁሉ ለምናቀርበው ጥያቄና ለምናሰማው ድምጽ መጀመሪያ ሆዳችሁን ሙሉ የሚል ምላሽን ስናገኝ ኖረናል፡፡

ዛሬ ግን የአድዋ ድል በተገቢው ቦታው ላይ እንዲነግስ የሚያስችል አኩሪ ታሪክ መጻፍ የምንችልበት ደረጃ ላይ የደረስን ይመስላል። ኢትዮጵያ ዳግም ነጻነቷን ልታውጅ፤ በስንዴ ምርት ራሷን ችላ ወደ ውጭ ገበያ ልትልክ፤ ከስንዴ ለማኝነት ወደ ስንዴ ላኪነት ልትሸጋገር ዳር ዳር እያለች ነው፡፡ ሀገሪቱ በዓለም ላይ ስንዴ ሸማች ከሆኑ ሀገራት ውስጥ በግንባር ቀደምትነት የምትታወቅ ስትሆን፤ በየዓመቱም እስከ 107 ሚሊዮን ኩንታል ስንዴ በማስገባት 1 ቢሊዮን ዶላር የሚጠጋ ወጪ ስታወጣ ቆይታለች፡፡

ባለፉት አራት ዓመታት መንግስት ለስንዴ ምርት በሰጠው ትኩረትም ኢትዮጵያ ስንዴን ከውጭ ማስገባት ከማቆሟም በሻገር ወደ ውጭ መላክ ጀምራለች፡፡ ይህ ጥረቷም በዓለም ላይ ስንዴ በማምረት ተጠቃሽ ከሆኑ 18 ሀገራት ተርታ ያሰልፋታል፡፡ ኢትዮጵያ ከስንዴ ተቀባይነት ወደ ስንዴ ላኪነት እራሷን በመለወጥም ታሪክ ሰርታለች፤ ለቀጠናው ሀገራትም ኩራትና ተስፋ ሰርቶ የመለወጥ ተምሳሌትም ሆናለች፡፡

ኢትዮጵያ እንደ ስንዴው ሁሉ ለሩዝ ምርት ትኩረት በመስጠት ከሀገራዊ ፍጆታ አልፎ ለውጭ ገበያ ለመላክ በትኩረት በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡ በተለይም ሀገሪቱ ለሩዝ ምርት ተስማሚ የሆነ የአየር ጸባይና ምቹ መሬት ያላት መሆኑ ያቀደችውን ወደ ተግባር ለመለወጥ እንደማያዳግታት የዘርፉ ምሁራን ያስረዳሉ። ከግብርና ሚኒስቴር የተገኘው መረጃ እንደሚያመለከትውም በኢትዮጵያ 5 ነጥብ 6 ሚሊዮን ሄክታር በሩዝ መልማት የሚችል መሬት ቢኖርም በየዓመቱ ከ200 ሺህ ቶን በላይ ሩዝ ወደ ሃገር ውስጥ በማስገባት በየዓመቱ 200 ሚሊዮን ዶላር ወጭ ታደርጋለች፡፡

በኢትዮጵያ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ስርዓት መተግበር ከጀመረ ካለፉት አምስት ዓመታት ወዲህ መንግስት ፊቱን ወደ ሩዝ ምርት በማዞር በአጭር ጊዜ ውስጥ አበረታች ውጤቶች መመዝገብ ጀምረዋል፡፡ ከሩዝ አኳያ አምና ከስምንት ሚልዮን ኩንታል ያልበለጠ ነበር የተመረተው ዘንድሮ በአንጻሩ 38 ሚልዮን ኩንታል ማምረት ተችሏል። በተለይ በአማራ ፎገራና በጅማ እንዲሁም በሶማሌ ክልል እየተከናወነ ያለው የሩዝ ምርት ኢትዮጵያን ከሩዝ ተቀባይ ሀገርነት ወደ ላኪነት የሚያሸጋግራት ነው፡፡

በፍራፍሬ ዘርፍም ተስፋ ሰጪ ስራዎች እየተከናወኑ ነው፡፡ እነዚህ ተስፋ ሰጪ ተግባራት ኢትዮጵያ በአጭር ግዜ ውስጥ ከተረጂነት ተላቃ እራሷን በምግብ እንደምትችል አመላካቾች ናቸው፡፡ መንግስት «ተረጂነት ይብቃ» በሚል መርህ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ ከተመጽዋችነት ለማላቀቅ አዲስ ዕቅድ ይዞ መጥቷል፡፡ በሚቀጥሉት ሁለት ዓመታት ውስጥ እስከ 250 ሺ ሄክታር በማረስ ኢትዮጵያ በቂ እህል ለማምረትና ከእርዳታ ተቀባይነት ለመላቀቅ አቅዳ እየሰራች ነው፡፡

ለዚህ ደግሞ አርሶ አደሩ ብቻ ሳይሆን ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከእርዳታ እሳቤ እራሱን ማውጣትና እራስን በምግብ ለመቻል የሚደረገውን ጥረት ሊያግዝ ይገባል፡፡ ሁሉም እርዳታ መቀበልን ከተጸየፈ ኢትዮጵያ ከተረጂነት ወደ ሰጪነት የምትሸጋገርበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም። በአጠቃላይ በለውጡ ዘመን በግብርና ምርታማነት ላይ የተሰሩት ስራዎች ነገን በተስፋ እንድንጠብቀው የሚያደርገን ነው፡፡

በለውጡ መባቻ ዘመን በኢትዮጵያ በአጠቃላይ የነበረው የምርት መጠን 300 ሚሊዮን ኩንታል ሲሆን በአምስት ዓመታት ውስጥ ወደ 600 ሚሊዮን ኩንታል ሊያድግ ችሏል፡፡ በ2017 መጨረሻም ከ800 ሚሊዮን ኩንታል በላይ የሚጠበቅ ሲሆን በ2018 የምርት ዘመን ወደ 1 ቢሊዮን ኩንታል እንደሚደርስ ይጠበቃል፡፡ ይህም ኢትዮጵያ በምግብ እራሷን እንድትችል ከማድረጉም በሻገር ስንዴ፤ ሩዝ እና የፍራፍሬ ምርቶችን በስፋት ለዓለም ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል አቅም የሚፈጥርላት ይሆናል፡፡

እንደ ግብርና ስራው ሁሉ የኢትዮጵያን ነገ ከሚያሳምሩት ውስጥ በኃይል አቅርቦት በኩል የተሰራው ስራ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ የአባይ ግድብ የስራ አፈጻጸም ነገን ቀና ብለን እንድንመለከት የተስፋ ወጋገን ያጎናጸፈን ነው። የአባይ ግድብ የኢትዮጵያውያን የአንድነት ማህተም ነው፡፡ ሆኖም ይህ ግዙፍ ግድብ በነበረው የአሰራር እና የአመራር ብልሽት ወደ መስተጓጎሉ ደርሶ ነበር፡፡ በኢህአዴግ የመጨረሻ ዘመናት ጀምሮ ግድቡ ሲመራበት የነበረው ሂደት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋልጦ የነበረ በመሆኑ በሂደት ግንባታው የሚቆምበት እድል የሰፋ ነበር፡፡

እንደ ዕድል ሆኖ በኢትዮጵያ የመንግስት ለውጥ እውን በመሆኑ የግድቡ ግንባታ ከመስተጓጎል ሊተርፍ ችሏል፡፡ በአሁኑ ወቅትም የሲቪል ስራው በመጠናቀቅ ላይ የሚገኝ ሲሆን የኤሌክትሮሜካኒካል ስራውም እየተፋጠነ ነው። በዚሁ ጉዳይ ላይ ሰሞኑን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) እንደገለጹትም «ዛሬ የሕዳሴ ግድብ ወደ ኋላ ከ205 እስከ 210 ኪሎ ሜትር ተኝቷል። ዛሬ የሕዳሴ ግድብ ወደታች ጥልቀቱ መቶ 133 ሜትር ደርሷል።

ዛሬ ሕዳሴ ግድብ የጣናን ሀይቅ እጥፍ አድጓል። ጣና እስከ 30 ቢሊዮን ነው። ይሄ 62 ነጥብ አምስት ነው፤ ደብል አድርጓል። የጣና ውሃ ስፋቱ ብቻ ሳይሆን በጣም ሻሎው ነው። 13፣ 14 ሜትር ነው ጥልቀቱ። ይሄ 133 ገደማ ሜትር ጥልቀት አለው። በጣም ጥልቅ ነው ማለት ነው። ወደታችም ወደኋላም ወደጎንም በጣም ሰፊ ስለሆነ የጣናን እጥፍ/ደብል ውሃ ሆኗል።» ሲሉ የአባይ ግድብ የደረሰበት ደረጃ አብራርተዋል። ይህ ደግሞ የአባይ ግድብ ዛሬን አድምቆ ነገን ብርሃን ፈንጥቆ የኢትዮጵያን ብልጽግና ለማወጅ መዘጋጀቱን የሚያመላክት ነው፡፡

ሌላኛው ከዛሬ አልፎ የነገ ተስፋ የሆነን ኢትዮጵያ በሰላማዊ መንገድ የባሕር በር ባለቤት ለመሆን እየሄደችበት ያለው መንገድ ፍሬ እያፈራ መምጣቱ ነው፡፡ በኢትዮጵያ አዲስ የመንግስት ለውጥ ከመጣ ጀምሮ በትኩረት ከሰራባቸውና ለውጥ ካመጣባቸው ጉዳዮች አንዱ የባሕር በር ጥያቄ ነው፡፡ መንግስት በኢትዮጵያውያን ዘንድ ለዘመናት ቁጭት ፈጥሮ የነበረውን የባሕር በር ጣያቄ በመመለስና ስብራትን በመጠገን ታሪካዊ ሚናውን እየተወጣ ይገኛል፡፡ለ27 ዓመታት ያህል ፈርሶ የቆየውን የባሕር ኃይል እንደገና በማደራጀት ኢትዮጵያ እንደገና የባሕር ኃይል እንዲኖራት አድርጓል፡፡

ከዚሁ ጎን ለጎንም ኢትዮጵያ ከ33 ዓመታት በኋላ የባሕር በር የምታገኝበት አማራጭ ተገኝቷል፡፡ ሰላማዊ አማራጭን ሲከተል ቆየው የኢትዮጵያ መንግስት ሰሞኑን ከሶማሊ ላንድ ጋር የባሕር በር የሚገኝበትን መግባቢያ ሰነድ (Memorandum of understanding) ተፈራርሟል፡፡ ይህ የመግባቢያ ሰነድ ሲተገበር አካባቢያዊ መረጋጋት የሚያመጣና ኢትዮጵያም በቀጣናው ላይ አለኝ የምትለውን የባለቤትነት ጥያቄ መልስ እንዲገኝ በር የሚከፍት ነው። ቀጠናዊ ሰላምን በማስፈን የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ የተረጋጋ እንዲሆን በር ይከፍታል፡፡

ሌላኛው የነገን ተስፋ ብሩህ ከሚደርጉት ሀገራዊ ክንውኖች ውስጥ አንዱና ዋነኛው የአረንጓዴ መርሃ ግብር ነው፡፡ የአረንጓዴ አሻራ መርሃ ግብር በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ዐቢይ አሕመድ አነሳሽነት እየተተገበሩ ካሉ ፕሮግራሞች አንዱ ነው። በየዓመቱም በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ የሚሳተፍበት ሀገራዊ ንቅናቄ ለመሆን በቅቷል፡፡ ሰሞኑን ይፋ በተደረገው የኢትዮጵያ የደን ሽፋን ሪፖርት እንደተመላከተው የኢትዮጵያ የደን ሽፋን በ2011 ዓመተ ምህረት ከነበረበት 17 ነጥብ 2 በመቶ አሁን በ2016 ዓ.ም ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ ከፍ ብሏል።

እዚህ ደረጃ ላይ መድረስ የተቻለው በኢትዮጵያ በየዓመቱ ከ30 ሚሊዮን ሰዎች በላይ የሚሳተፉበት የችግኝ ተከላ በማካሄድ ነው። የችግኝ ተከላው በአንድ ጀንበር በሚሊዮኖች የሚተከሉ ችግኞችን በመትከል ዓለም አቀፍ እውቅና ማትረፉን ጭምር ያካተተ ነው። ለዚህም ባለፈው ነሃሴ 17 ቀን 2016 ዓ.ም በአንድ ጀንበር 615.7 ሚሊዮን ችግኝ በመትከል ቀደም ሲል በራሳችን ተይዞ የነበረውን ዓለም አቀፍ ሪከርድ ማሻሻል ችለናል፡፡

ከእነዚህ ግዙፍ ስራዎች ጎን ለጎንም በቱሪዝም፤ በኮሪደር ልማት፤ በዲፕሎማሲ፤ ጠንካራ ሀገራዊ ሰራዊት በመገንባት እና በመሳሰሉት ዘርፎች እየተሰሩ ያሉ ስራዎች ነገን በተስፋ አሻግረን እንድንመለከት የሚያደርጉን ናቸው፡፡ ከወዲሁም ባለፉት አምስት ዓመታት በተሰሩ ስራዎች ዛሬ ኢትዮጵያ በምስራቅ ቀዳሚዋ የግዙፍ ኢኮኖሚ ባለቤት ለመሆን በቅታለች። ተጽዕኖ ፈጣሪነቷም እያደገ መጥቷል። ይህ ደግሞ አሁን ላለነውም ሆነ ለልጆቻችን ነገን ብሩህ ቀን የሚያደርግ ጅማሬ ነው፡፡

**አብዝቶ እንደሚነገረው፤ በተጨባጭም እንደሚታየው፤ ነገ የዛሬ ውጤት ነው፡፡ የዛሬ ትጋትም የነገ ትሩፋት ነው። ኢትዮጵያውያን ዛሬ ላይ በለውጥ/መለወጥ መንፈስ ተነቃቅተው እየሰሩት ያለው ስራ እና በተጨባጭ እየታየ ያለው ውጤት ነገን በተስፋ እንድንጠብቅ ልብን ሙሉ የሚያደርግ፤ ሀገራዊ ብልጽግናውም አይቀሬ እንደሆነ አመላካች ነው**

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

## ዲጅታላይዜሽን-የመጪው ጊዜ ብሩህ ተስፋ

**ወርቅነሽ ደምሰው**

የ13 ወራት ባለጸጋ የሆነችው ኢትዮጵያን ከሌላው ዓለም ለየት ከሚያደርጓት ወራት መካከል አንዷ የጳጉሜ ወር ናት፡፡ ኢትዮጵያውያንም በየዓመቱ አምስት ቀናት እንዲሁም በአራት ዓመት አንድ ጊዜ ደግሞ ስድስት ቀናት ያሏትን ወርሃ ጳጉሜን በተለያዩ ስያሜዎች ማክበር ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል፡፡ በመሆኑም ጳጉሜ 5 ቀን 2016 ዓ.ም ‹‹የነገ ቀን›› የሚል ስያሜን "የዛሬ ትጋት፤ ለነገ ትሩፋት" በሚል መሪ ሃሳብ እየተከበረ ይገኛል፡፡

እኛም ይህንኑ ሃሳብ መሰረት በማድረግ በዛሬው የሳይንስና ቴክኖሎጂ አምዳችን ኢትዮጵያ አሁን ላይ የዲጂታል ዓለምን ለመቀላቀል የምታደርጋቸው ጥረቶችና ይህን ተከትሎ እየተገኙ ያሉ ስኬቶች ለነገ ወይም ለመጪው ትውልድ ምን ያህል ትሩፋትና ተስፋ ሊሆኑ እንደሚችሉ ቃኝተናል፡፡

አደጉና በለጸጉ የሚባሉት አገራት ወደ ተራቀቀ የቴክኖሎጂ ጥግ ለመድረስ በፍጥነት እየገሰገሱና እየተሽቀዳደሙ ባሉበት በዚህ ‹‹በዘመነ ዲጂታላይዜሽን›› ዲጂታል ቴክኖሎጂ ለሰው ልጅ እንደ ምግብ፣ ልብስና መጠለያ ሁሉ መሠረታዊና አስፈላጊ እየሆነ መጥቷል፡፡ እኛም በዚህ መጠን አስፈላጊነቱ እየጨመረ ከመጣው ዲጂታል ቴክኖሎጂ ውጪ መሆን የማይታሰብበትና የማይቻልበት ደረጃ ላይ እየደረስን እንገኛለን፡፡

ቀድመው የዲጂታሉን ዓለም እየመሩ ያሉት የበለጸጉት አገራት ዲጂታል ኢኮኖሚን በመገንባት የኢኮኖሚ አቅማቸውን እያሳደጉ ከፍተኛ ሀብት እያከማቹ ይገኛሉ፡፡ የዲጂታል ቴክኖሎጂ እንዲህ የዓለም ከፍተኛ ሀብት እያንቀሳቀሰ ኢኮኖሚውን እየመራ ባለበት በዚህ ዘመን ከዚህ ሀብት አለመጠቀምና ከዲጂላይዜሽን እሳቤ ውጪ መሆን የማይታሰብ ነው፡፡ የማይታሰብ ብቻ ሳይሆን ዲጂታላይዜሽን ውስጥ ተሳታፊ መሆን አለመቻል በራሱ ከዓለም ወደኋላ ቀርቶ እንደመጓዝ ይቆጠራል።

በሌላ በኩል ዲጂታላይዜሽን ከመቀላቀል ጋር ተያይዘው የሚነሱ ስጋቶች አሉ፡፡ ስጋቶች ቢኖሩም ‹‹ህልም ተፈርቶ ሳይተኛ አይታደርም›› እንደሚባለው ሁሉ ቀድሞ ተዘጋጅቶ ስጋቶችን መመከት የሚያስችል አሠራር በመዘርጋት ከዓለም ጋር አብሮ ወደፊት መጓዝ የግድ ነው፡፡ በተለይ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ዲጂታላይዜሽንን ማስፋፋት ተከትሎ የሳይበር ደህንነት ጉዳይ የዓለማችን ቀዳሚ ስጋት እየሆነ ቢመጣም ከቴክኖሎጂው ውጪ መሆንም ስለማይቻል በዚያው ልክ ትኩረት ሰጥቶ መስራት ያስፈልጋል፡፡

መረጃዎች የሚያመላክቱትም ዲጂታላይዜሽን መስፋፋትን ተከትሎ የሳይበር ደህንነት ስጋት ከጊዜ ወደ ጊዜ እየጨመረ በዓለም አቀፍ ደረጃ የሳይበር ጥቃቶች የሚያስከትሉት ኪሳራ እየተበራከተ መምጣቱን ነው፡፡ በዚህም በዓለም አቀፍ ደረጃ እ.ኤ.አ በ2023 ስምንት ትሪሊዮን ዶላር የሳይበር ጥቃት ኪሳራዎች የደረሱ ሲሆን፤ እ.ኤ.አ በ2025 ዐሥር ትሪሊዮን ዶላር ኪሳራ ሊደርስ ይችላል ተብሎ ይገመታል፡፡

በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገራት ዲጂታላይዜሽንን በመቀላቀል ዲጂታል ኢኮኖሚ በመገንባት ዓለም የደረሰበት ለመድረስ በፈጠነ ሁኔታ ወደፊት መጓዝ የሚያስችላቸውን አካሄድ በመከተል ብዙ መስራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ኢትዮጵያም ይህንኑ ቀድመው በመረዳት ዲጅታላይዜሽንን በፍጥነት ተቀላቅለው ተግባራዊ እያደረጉ ካሉ አገራት መካካል ትመደባለች፡፡

የዲጂታል ኢኮኖሚን በመገንባት ረገድ የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) ዘርፉን ትኩረት ተሰጥቶት ከአምስቱ ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያዎች አንዱ ምሰሶ ተደርጎ እየተሰራ ይገኛል፡፡ ዲጂታል ኢትዮጵያም 2025 ስትራቴጂ የዚሁ አንዱ አካል ነው፡፡

በቅርቡም የዲጂታል ኢትዮጵያ አስፈላጊነት አስመልክቶ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) እንደተናገሩት፤ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ እንዲኖርና በሁሉም ተቋማት ተሰናስሎ እንዲመራ ያስፈለገበት ዋና ምክንያት ቀደም ሲል እንደሀገር የነበረው ችግር ለመወጣት በማሰብ ነው፡፡ ከዚህ ችግር ለመውጣት ወጣ ያለ አስተሳሰብና አሰራር በመከተል ዲጂታል ኢኮኖሚን ተግባራዊ ማድረግ አስፈልጓል፡፡

እሳቸው እንዳሉት፤ ይህም ከዚህ ቀደም ሲል የነበረውን እሳቤና ልምምድ የሚቀይር ነው፡፡ ለአብነትም ቀደም ሲል አንድ ኩባንያ በሁሉም ኢንዱስትሪዎች ውስጥ ቢሳተፍ በቢሊዮን የሚቆጠሩ ዶላሮች ለማግኘት ቢያንስ 20 ዓመታት ይፈጅበታል፡፡ በዲጂታል ኢንዱስትሪው ውስጥ ግን አብዛኞቹ ኩባንያዎች ቢሊዮን ዶላር በአራት ዓመት ውስጥ ያገኛሉ፡፡ ይህም አንደኛ በፍጥነት ገንዘብ ያስገኛል፡፡ ሁለተኛው በርካታ ሀብት ይገኝበታል፡፡ እንደ ሀገር ኢትዮጵያ ደግሞ ሰፋ ያለ የሰው ሀብት ስላላት ይህንን ዘርፍ በተወሰነ ደረጃ መጠቀምና ዲጂታል ኢኮኖሚውን እንደ አንድ ምሰሶ ወስዶ መስራት ካልተቻለ የሚታሰበውን ማሳካትና የታለመውን ለውጥ ማረጋገጥ አይቻልም ከሚል እሳቤ በመነሳት ዲጂታል ዘርፍ ከኢኮኖሚ ዋና ዋና ምሰሶዎች አንዱ ሆኖ እንዲሰራበት ተደርጓል፡፡

ይህ ዘመን ዲጂታል ኢኮኖሚ መገንባትን ይጠይቃል፡፡ በዓለም ላይ አሁን ካሉ አሥር ሀብታም ኩባንያዎች ከአንደኛ እስከ ስድስተኛ ደረጃ የያዙት በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ የሚሰሩ ናቸው፡፡ ከዚህ የሚበልጠው ደግሞ ሰባተኛ፣ ስምንተኛ፣ ዘጠነኛና አስረኛ ደረጃ የያዙት ተራ ኩባንያዎች አይደሉም። ለምሳሌ እንደ ቴስላ፣ ቪዛ ካርድ እና ትልቁ የሳውድ አረቢያ የነዳጅ ኩባንያ ጨምሮ ከስድስቱ በታች ባሉ ደረጃዎች ላይ ይገኛሉ። እነዚህ አራቱ ኩባንያዎች ያከማቹት ሀብት ተደምሮ አንደኛና ሁለተኛ ደረጃን የያዙት ሁለቱ ኩባንያዎች ያከማቹትን ሀብት አያህልም፡፡ ይህ የሚያሳየው አብዛኛው ሀብት ያለው በዲጂታል ኢኮኖሚ ዘርፍ መሆኑን ነው ሲሉ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ተናግረዋል።

ለዚህ መንግሥትም በሀገር በቀል ኢኮኖሚ ማሻሻያው ዲጂታል ኢኮኖሚ ለመገንባት የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) ዘርፍ አንድ መሠረት አድርጎ ወስዶ ዲጂታል 2025 ስትራቴጂም ተግባራዊ እየተደረገ ነው ብለዋል። የዲጂታል ስትራቴጂው አንዱ አቅጣጫ ደግሞ የዲጂታል ምህዳሩን በማስፋት ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመፍጠር አካታች የሆነ ከባቢን መፍጠርን ይጠይቃል፡፡ ይህ ደግሞ በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ መንግሥት ብቻ ተዋናይ ሆኖ መገኘቱ የሚገባውን ያህል ትርፍ ማግኘት አያስችልም፡፡ ስለዚህ አውዱን ማስፋት በዚህ ረገድ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል የግሉን ዘርፍ እንዲሳተፍ፣ ስታርትአፖችን እንዲስፋፉ ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ ተናግረዋል።

ሌላው የአእምሮ ዝግጁነት /ማይንድ ሴት/ ሊኖር ይገባል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ቀደም ሲል በመንግሥት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ችግሮችን መደርደርና ጽዱ ሆኖ አለመገኘት እንደጥሩ ባህል የሚታይና የተለመደ እንደነበር ይገልጻሉ፡፡ ይህ አሰራር በመቀየር ቢሮዎችና የሥራ አካባቢዎች ንጹሕ ማድረግ እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡ እነዚህና መሰል ሳንካዎችን ተራምደን እንዳንሄድ ያሰሩን ነገሮች ካልተነቀሉ በስተቀር በዲጂታል ዘርፉ የሚጠበቀውን ለውጥ ማምጣት አይቻልም፡፡ ይህ ደግሞ መለወጥ ብቻ ሳይሆን በዚህ ረገድ አሁን ድረስ ሰፊ ሥራ መስራትን ይጠይቃል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

ይህንንም ሲያስረዱ ኢትዮጵያ አምስተኛ ትውልድ የሞባይል ኔትዎርክ ኢንተርኔት 5ጂ ጥቅም ላይ ስታውል አብዛኛው ሰው እንደቅንጦት ሊያየው ይችላል፡፡ ነገር ግን ይህ ለኢትዮጵያ በእጅጉ የሚያስፈልገን እና የዲጂታል ኢኮኖሚን ለመቀላቀል የሚያስፈልጉ አስቻይ ሁኔታዎች አንዱ እንደሆነ መታወቅ አለበት፡፡ ዲጂታል ኢትዮጵያን እውን ለማድረግ ሊኖሩ ከሚገባቸው አስቻይ ሁኔታዎች መካከል የመጀመሪያው ኢነርጂ ነው፡፡ ሁለተኛው ዳታ ሲሆን ሦስተኛው ዲጂታል መታወቂያ ነው፡፡ እነዚህ በእጅጉ የዲጂታልን ለመቀላቀል አጋዥ እንደሆኑ አስረድተዋል፡፡

በሌላ በኩል ወደ ዲጂታሉን ዓለም ስንቀላቀል ስጋት የሆኑ ነገሮች ስላሉ እነዚያን ቀድሞ አውቆ ለዚያ ዝግጅት ማድረግን ይጠይቃል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ በየቀኑ በሺዎች የሚቆጠሩ የሳይበር ጥቃቶች ይሰነዘራሉ። ጥቃቱም እንዳለ ሆኖ ግን የመከላከል አቅሙም አብሮ እያደገ ሄዶ ሀብቶችን እንዳይጠፉ መከላከል እንደሚያስፈልግ ይገልጻሉ፡፡

እንደ ጠቅላይ ሚኒስትሩ ማብራሪያ፤ በዲጂታሉ ዘርፍ ለምሳሌ ሰው ሰራሽ አስተውሎት /አርተፊሻል ኢንተለጀንስ/ ወስደን አሁን ላይ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች ብንመለከት እኛ ዛሬ የምንሰራቸው መሰረቶች አሁኑ የሚታዩ አይደሉም፡፡

ሰው ሰራሽ አስተውሎት እኤአ በ2030 በዓለም አጠቃላይ ምርት /ጂዲፒ/ ላይ 16 በመቶ እድገት ያመጣል። ይህ ማለት ደግሞ ሰው ሰራሽ አስተውሎት 15 ትሪሊዮን ተጨማሪ ሀብት ያስገኛል፡፡ ይህን ሀብት የሚቀራመቱት ግን ጥቂት አገራት ናቸው፡፡

> **በዲጂታል ኢኮኖሚ ውስጥ መንግሥት ብቻ ተዋናይ ሆኖ መገኘቱ የሚገባውን ያህል ትርፍ ማግኘት አያስችልም፡፡ ስለዚህ አውዱን ማስፋት ያስፈልጋል፤ በዚህ ረገድ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎችን አጠናክሮ በመቀጠል የግሉን ዘርፍ እንዲሳተፍ እንዲሁም ስታርትአፖች እንዲስፋፉ ማድረግ ያስፈልጋል**

ከኢትዮጵያ አንጻር ያለው እሳቤ ልክ እንደ መኪናና አውሮፕላን ያሉ መገልገያዎችን ለማስገባት የነበረው ትግል መቀነስን የሚጠይቅ መሆኑን ጠቅሰው፤ ስለጉዳዩ የሚወያዩ፣ የሚያነቡ፣ የሚማሩ እና የሚሞክሩ ልጆች መፍጠር ሲቻል ከዚያ ትልቁ ሀብት ትንሽዬ ድርሻ ማግኘት ያስችላል በማለት አብራርተዋል፡፡

የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ካውንስልን በበላይነት የሚመሩት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ተመስገን ጥሩነህ በአንድ ወቅት የዲጂታል ኢኮኖሚ መገንባት ለሀገር ልማት የሚያመጣውን ቱሩፋት አስመልክተው ማብራሪያ መስጠታቸው ይታወሳል።

እሳቸው እንዳሉት፤ ኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ ትልቅ ትኩረት ሰጥታ እየሰራች ትገኛለች፡፡ በሁሉም ዘርፎች ላይ የቴክኖሎጂ አስፈላጊነት እጅግ ከፍተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ ከዕለት ተዕለት ኑሮ ጋር እጅግ የተሳሰሩ የቴክኖሎጂ አማራጮች እንዳሉ ሆነው አጠቃላይ አገራዊ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን ለማሳለጥ የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሰሩ ነው፡፡ ይህ ደግሞ ቴክኖሎጂ ተጠቃሚ የኢኮኖሚ ዘርፍ በብዛት እንዲኖር አድርጓል፡፡ በዲጂታል ዘርፍ የተሰማሩ በርካታ ወጣቶች ራሳቸውን እያሳደጉ የሥራ እድልን እንዲፈጥሩ አስችሏል።

‹‹ዲጂታል ትራንስፎርሜሽንን ማሳደግ የመንግሥትን አገልግሎት ለማሳለጥ፣ ለማህበራዊ ተሳትፎ መጎልበት እና የስራ እድል ለመፍጠር ከፍተኛ ሚና አለው›› ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ፤ ለታዳጊ አገሮች ከድህነት ለመውጣት ኢኮኖሚን ለመገንባት ዘርፉ ትልቅ ኢኮኖሚ አመንጪ ነው። በተለይ እንደ ኢትዮጵያ ያሉ ታዳጊ አገራት ትልቁ ፈተና የመንግሥት አገልግሎቶች አሰጣጥ ግልጸኝነት የጎደላቸው፣ ተደራሽ ያልሆኑ እና ብዙ ችግሮች ያሉባቸው መሆናቸው ነው።

በመሆኑም ታዳጊ አገራት ቴክኖሎጂ እንደ ትልቅ መሳሪያ የሚጠቀሙት አገልግሎታቸውን ለማቀላጠፍ ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ እንዳብራሩት፤ ኢትዮጵያ ዲጂታል ኢኮኖሚን ለመገንባት ካሏት አስቻይ ሁኔታዎች መካከል አንደኛው በሕዝብ ብዛቷ የምትታወቅና ከዚህም ሕዝብ አብዛኛው ወጣት መሆኑ ነው። ወጣቱ ለቴክኖሎጂ ያለው መሰጠት እጅግ ከፍተኛ ነው፡፡ ሁለተኛው ሀገር በቀል የኢኮኖሚ ማሻሻያው ከአምስቱ (ከግብርና፣ ከማኑፋክቸሪንግ፣ ከቱሪዝም እና ከማዕድን) ዘርፎች ቀጥሎ የኢንፎርሜሽን፣ ኮሙኒኬሽንና ቴክኖሎጂ (አይሲቲ) እንደ አንዱ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት ነው፡፡ ይህም መሆኑ ኢኮኖሚን በማመንጨት የመንግሥት አገልግሎትን በማዘመን፣ ለብዙ ዜጎች የስራ እድል መፍጠር ያስችላል፡፡

ሦስተኛው የመሠረተ ልማት እድገት ሲሆን መሠረተ ልማት በዳታ ተደራሽነትም ሆነ ከሌሎች አንጻር ሲታይ እያደገ መጥቷል፤ መንግሥት በፕራይቬታይዜሽን በሰጠው እድል መሠረት ሳፋሪኮም የተሰኘው ኦፕሬተር ወደ ሀገሪቱ ገብቶ እየሰራ መሆኑ ይታወቃል። ተጨማሪ ኦፕሬተሮች ዘርፉን እንዲቀላቀሉ እየተሰራ ይገኛል፡፡

ከመሠረተ ልማት አኳያም መንግሥት ትኩረት ሰጥቶ የማልማት ሥራ እየሰራ መሆኑን ጠቅሰው፣ መሰረተ ልማቱም በተሻለ ሁኔታ እየተስፋፋ መሆኑን ገልጸዋል፡፡ ከእነዚህ አንጻር ሲታይ ዲጂታል ኢትዮጵያን በማሳደግ የኢኮኖሚ ምንጭ በማድረግ፣ አገልግሎቶችን ማቀላጠፍ እንደሚቻል አስታውቀዋል።

ኢትዮጵያ ዲጂታል 2025 ትራንስፎርሜሽን ስትራቴጂን ቀርጻ እየሰራች ትገኛለች፡፡ ይህ ደግሞ በ2025 በአጠቃላይ ሁለንተናዊ በሆነ መልኩ በማህበራዊ እና በኢኮኖሚ የዲጂታል ኢኮኖሚ ዘርፍ እያሳደገች ከአፍሪካ ግንባር ቀደም ተጠቃሚ እንድትሆን የሚያስችል ነው ሲሉ አስረድተዋል፡፡

### እንደ መውጫ

በኢትዮጵያ የዲጂታል ኢትዮጵያ እውን የማድረጉ ጉዞ ተጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ዲጂታላይዜሽንን ማስፋፋትና ማሳለጥ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎችም እየተሰሩ ይገኛሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥ የመንግሥት አገልግሎቶችን በማዘመን ወደ ዲጂታል መቀየር፣ የክፍያ ሥርዓቶችን በኤሌክትሮኒክስ እንዲሆኑ ማስቻል እና ለዲጂታል ሥራዎች አጋዥ የሆኑ መተግበሪያዎች በልጸገው ስራ ላይ እንዲውሉ መደረጋቸውን ይጠቀሳሉ፡፡

ዲጂታል ቴክኖሎጂን እውን የማድረጉን ሂደት በቴሌኮም መሰረተ ልማት ግንባታ፣ በሲስተሞች ልማት፣ በአስቻይ ምህዳር ፈጠራ እና በሰው ሀብት ልማት ረገድ የዲጅታል ኢትዮጵያ ጉዞ መደላድል የሚሆኑ ሥራዎችን በመስራት የሚታዩ ለውጦች እየመጡ ናቸው ማለት ይቻላል፡፡

መንግስት ይህን ለውጥ ለማስቀጠል አሁንም መስራቱን አጠናክሮ ቀጥሏል፡፡ ወጣቶች በዘርፉ ያላቸውን ሚና በመረዳት መንግስት የተለያዩ ተግባሮችን እያከናወነ ሲሆን፣ አምስት ሚሊየን ወጣቶች በኮዲንግ ስልጠና እንዲከታተሉ ከተባበሩት አረብ ኢምሬቶች መንግስት ጋር ያደረገው ስምምነትና እሱን ተከትሎ መስጠት የጀመረው ስልጠናም ለእዚህ በአብነት ይጠቀሳል፡፡

‹‹ዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ስትራቴጂ›› ጸድቆ ተግባራዊ ከተደረገ ሦስት ዓመታትን አስቆጥሯል፡፡ ከተጀመረ አጭር ጊዜ ቢሆንም የዲጂታል ቴክኖሎጂን ተደራሽነትን በማስፋፋት ረገድ ብዙ ሥራዎች እየተሰሩ ለውጦች እየታዩ ነው፡፡ በተለይ የዲጂታል ፋይናንስን በማሳደግ ረገድ እየተሰሩ ያሉ ሥራዎች አበረታች ውጤቶች እያስመዘገቡ ይገኛሉ፡፡

የዲጂታል ትራንስፎርሜሽን ገና በጅማሮ ላይ ያለ እንደመሆኑ፣ የተለያዩ ችግሮችና ተግዳሮቶች ያሉበት ቢሆንም ዲጂታል ሥርዓትን በማስፋት በተለይ የኤሌክትሮኒክስ ግብይትና የክፍያ ሥርዓት ተግባራዊ እንዲሆኑ መደረጉ ለውጦች እንዲመጡ ውጤቶች እንዲመዘገብ ያስቻሉ ስለመሆናቸው የዘርፉ ባለሙያዎችም ይመሰክራሉ፡፡ ይህም ጤናማ የዲጂታል ፋይናንስ በማስፈን ለዲጂታል ትራንስፎርሜሽን እውን መሆን መሠረት የሚጥል በመሆኑ ዲጂታል ኢትዮጵያ እውን እንዲሆን ሁሉም የድርሻውን መውጣት እንዳለበት ይመክራሉ፡፡

ፖለቲካና ወቅታዊ

# ወቅታዊ ትንታኔ

## ስለነገ ሰላም - ቁልፉ ነገር

**ምሕረት ሞገስ**

በሺህ የሚቆጠሩ ዓመታትን መሻገሯ የሚነገርላት ኢትዮጵያ፤ ትናንት ሰላማዊ እና የበለፀገች አገር እንዳትሆን ያደረጓት ምክንያቶች እንዲሁም ነገ ከዛሬ በተሻለ ሰላም እንድትሆን መሠራት ስላለበት ጉዳይ ፖለቲከኞች እና የአገር ተቆርቋሪዎች የተለያዩ ሃሳቦችን ይሰነዝራሉ። የኦሮሞ ፌዴራላዊ ኮንግረስ (ኦፌኮ) የኦዲት እና ኢንስፔክሽን ፀሃፊ፤ የአንድነት መድረክ ዋና ፀሃፊ እና የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ደስታ ዲንቃ እንደሚናገሩት፤ ኢትዮጵያ ከጥንት ጀምሮ ሰላም እንዳትሆን ምክንያት የሆነው መንግስታት የሕዝብን ጥያቄ በበቂ መጠን ስለማይመልሱ ነው ሲሉ፤ የአባይ ንጉሶች ሚዲያ ባለቤት እና ከዓረቡ ዓለም ጋር በተለይም በዓባይ ጉዳይ ላይ እየተሟገቱ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር እየሠሩ የሚገኙት አቶ ጀማል በሽር በበኩላቸው የኢትዮጵያ የሰላም ማጣት መንስኤ መሃይምነት ነው ይላሉ፡፡

አቶ ደስታ በኢትዮጵያ ውስጥ ዜጎች፣ የተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ጨምሮ የተለያዩ ቡድኖች ለጥያቄያቸው መልስ ማግኘት ባለመቻላቸው ሕግን በራስ ለማስፈፀም እና የሚፈልጉትን መብታቸውን በጉልበት ወደ ማስጠበቅ አዝማሚያ ይሔዳሉ፡፡ የሕዝብ አመፅም ሆነ ጠብመንጃ ይዞ ጫካ መግባት የዚሁ አካል ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለዘመናት ኢትዮጵያ ሰላም እንዳትሆን ምክንያት ሆኗል ይላሉ፡፡

አቶ ጀማል በበኩላቸው፤ የግጭቶች መንስኤዎች ወይም ሰላም የጠፋበት ዋነኛዎቹ ምክንያቶች መሃይምነት ነው የሚል እምነት አላቸው፡፡ ከመሃይምነት ባሻገር ትንሽ የተማሩ እና ያወቁ ደግሞ ሆን ብለው ግጭትን የሚሠሩ እና ግጭቶችን የሚያባብሱ መሆናቸውን ይናገራሉ፡፡ ይህንን የሚያደርጉበት የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሏቸው በመጠቆም፤ አንደኛው እና ዋነኛው ስልጣን ፍለጋ መሆኑን ያስረዳሉ፡፡

ስልጣን ፈላጊዎች መሃይሞችን ተጠቅመው ራሳቸውን ወደ ስልጣን ለማምጣት አጭሩ መንገድ ብለው የሚመርጡት ጦርነት እና የግጭት መንገድ መሆኑን የሚያብራሩት አቶ ጀማል፤ ከዚሁ ጋር አብረው የሚያነሱት ሃሳብ ስልጣን ፈላጊዎች ምንም እንኳ ዓላማቸው ስልጣን ቢሆንም በመሃይምነት ውስጥ ያለው ኅብረተሰብ በመንጋ እንዲከተላቸው ይፈልጋሉ። ለእዚህም ኅብረተሰቡን የሚያነሳሱበት መንገድ የድሮ ትርክትን በመጥቀስ የኅብረተሰቡን ቁስል በመነካካት መሆኑን ይናገራሉ፡፡

አንዳንዴ የሚያነሷቸው ታሪኮች ፈጠራ ላይ የተመሠረቱ መሆናቸውን በመጠቆም፤ እውነት ላይ የተመሠረቱ ቢሆኑ እንኳ፤ አሁን ላይ ምንም ሊባልበት የማይችል፤ የድሮ ሰዎች ዕዳውን ከፍለው የጨረሱትን ነገር ስቦ በማምጣት ሰዎች እንዲዳከሩበት እና ዕዳ እንዲከፍሉበት የሚጠቀሙበት ሂደት መሆኑንም አቶ ጀማል አብራርተዋል፡፡

እንደ አቶ ጀማል ገለፃ፤ እዚህ ላይ አብሮ ዘረኝነት ይወለዳል፡፡ የእከሌ ዘር በአንተ ላይ ተጠቅሟል፤ አንተ ተጎጂ ነህ የሚሉና የመሳሰሉ የተለያዩ ከዘር ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ጉዳዮች በማንሳት የበላይ መሆን እና መምራት ያለብህ አንተ ነህ በሚል ግጭት ለማስነሳት ይጥራሉ፡፡

በተጨማሪ በአቶ ጀማል የተነሱት፤ የኖረ አንዳንድ ጀብደኝነትን የሚያሳይ ተንኳሽ እሳቤዎችን ከዘረኝነት ጋር ቀላቅሎ የማንሳት ዝንባሌ አለ የሚል አንደኛው ሲሆን፤ በሌላ በኩል ስልጣን በፍፁም በሕጋዊ መንገድ ሰዎች ማግኘት እንደማይችሉ እና መንገዱ የተዘጋ መሆኑን በማሳመን፤ በፀብ አጫሪነት ወይም በጦርነት እና በግጭት ካልሆነ በስተቀር ፈፅሞ የሚፈለገው እንደማይገኝ የመንገር ዝንባሌ በራሱ ለሰላም መደፍረስ ሌላኛው መንስኤ መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ግጭት እና ጦርነት ላይ የሚያተኩሩ እና ግጭት እንዲፈጠር የሚቀሰቅሱ በምርጫም ሆነ በሕጋዊ መንገድ ወደ ፊት መጥቶ ስልጣን የመያዝ አቅም እንደሌላቸው የሚያውቁ ሰዎች መሆናቸውን በመጠቆም፤ ያለውን ጥሩ የሆነውንም ሆነ መጥፎ የሆነውን መንገድ በትክክል ከማሳየት ይልቅ መንግስት ላይ ጦርነት በመፍጠር ወይም ከተለያዩ አካሎች ጋር ግጭት ውስጥ በመግባት ኢትዮጵያዊነት ልክ እንዳልሆነች ችግር እንዳለባት አስመስለው ለሕብረተሰቡ በማሳየት ሰዎች ወደ ጦርነት እንዲገቡ የሚኬድበት ሁኔታ ኢትዮጵያን ሠላም ሲያሳጣት እንደኖረም ነው አቶ ጀማል የተናገሩት፡፡

> **የነገዋ ኢትዮጵያ ሠላም እንዲሠፍንባት ዋናው እና ቁልፉ ነገር፤ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡ በቀጣይ ዓመት ሕግ እንዲከበር ከተሠራ ሰላም የማይኖርበት ምክንያት የለም**

የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ደስታ በበኩላቸው፤ ሕግን አክብሮ ማስከበር ዋናው የሰላም ምሰሶ መሆኑን ጠቁመው፤ በኢትዮጵያ ያለው ልማድ በተለያዩ ዘመናት መንግስታት ቢቀያየሩም ራሳቸው ከሕግ በላይ ሆነው ዜጎች ብቻ ሕጉን እንዲያከብሩ ያደርጋሉ፡፡ ይሔ ልማድ መቅረት አለበት ይላሉ፡፡ በአቶ ደስታ እምነት የኢትዮጵያ ሕዝብ አብዛኛው እንደውም ከ90 በመቶ በላይ ሕዝቡ ለሕግ ተገዢ፤ ራሱን ለማሳደግ እና ኑሮውን ለማሻሻል የሚባዝን ነው፡፡ በሌላ በኩል ልክ እንደርሳቸው ሁሉ የመንግስትን ሕግ አለማክበር እና አለማስከበር በተመለከተ ጥያቄ የሚያነሱ ዜጎች አሉ፡፡

ለአገራቸው እና ለሕዝባቸው የሚያስቡ ሕገወጥነትን መሸከም የማይችሉ የሕብረተሰብ ክፍሎች ጥያቄ ያነሳሉ። የሚያነሱት ጥያቄ ምላሽ ካላገኘ ጥያቄው ከእነርሱ አልፎ ወደ ወጣቱ እና ወደ ተለያዩ የሕብረተሰብ ክፍሎች በሚሔድበት ጊዜ ግጭት ተፈጥሮ ሁኔታው ወደ አለመግባባት ያድጋል፤ በዚህ ጊዜ በመንግስት እና በሕዝቡ መካከል ያለው ግንኙነት የተበላሸ ይሆናል፡፡ ይህ ደግሞ ለጦርነት እና ለግጭት ይዳርጋል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ደስታ ገለፃ፤ የነገዋ ኢትዮጵያ ሠላም እንዲሠፍንባት ዋናው እና ቁልፉ ነገር፤ የሕግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ማስቻል ነው፡፡ በቀጣይ ዓመት ሕግ እንዲከበር ከተሠራ ሰላም የማይኖርበት ምክንያት የለም፡፡ ሕግ መከበር አለበት ሲባል፤ በተወሰነ ሰው ብቻ ሳይሆን ከተራ ዜጎች ጀምሮ የመንግስት ቁልፍ ሰዎች እና የመንግስት ቁንጮዎችን ጨምሮ ሁሉም ከሕግ በታች መሆን አለባቸው፡፡

ሕግ ሲባል በዜጎች እና በዜጎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገዛ፤ በመንግስት እና በዜጎች መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገዛ፤ በመንግስት ተቋማት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚገዛ ሕገመንግስታዊ እና ሌሎች ሕጎች ማክበር ማለት መሆኑን በመጠቆም፤ በአገሪቱ የሚኖሩ ግንኙነቶች በሙሉ በሕግ እና በሕግ አግባብ መሆን አለባቸው፡፡ ሕግ እና ሕገመንግስቱ መከበር አለበት፡፡ ይህ ከሆነ የነገዋ ኢትዮጵያ ሰላም መሆኗ አይቀርም ይላሉ፡፡

አቶ ደስታ፤ ሁሉም ለሕግ በሚገዛበት ጊዜ መብት እና ግዴታ በአግባቡ ይጠበቃል፤ ሁሉም በደንብ እኩል ይከበራል፡፡ ሁሉም ሕግን ተከትሎ ግዴታውን ይወጣል፤ ሕግን ተከትሎ መብቱን ይጠይቃል፡፡ ስለዚህ ለነገዋ ኢትዮጵያ ብልፅግና፣ ሠላም እና መረጋጋት፤ ለግንኙነቶች ሠላማዊ መሆን ዋናው እና ቁልፉ ነገር ሁሉም አካላት ከሕግ በታች መሆናቸው ነው የሚል ፅኑ እምነት እንዳላቸው አስረድተዋል፡፡

የፖለቲካ ፓርቲዎች ሠላም ፈላጊ መሆን፤ መከባበር እና በመካከላቸው የሚደረጉ ውድድሮች በንግግር ላይ የተመሠረቱ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ የሰብአዊ መብቶችን ማክበር እና ለማስከበር መስራት፤ መብትን እና ግዴታን አውቆ በዛ ማዕቀፍ ውስጥ መንቀሳቀስ ሰላምን እና ብልፅግና ለማረጋገጥ መስራት ግድ የሚላቸው መሆኑንም አቶ ደስታ ያስረዳሉ፡፡

ዴሞክራሲያዊ መብቶች ባማረ መልኩ በሕገመንግስቱ ተቀምጠዋል ካሉ በኋላ፤ የመንግስት ስልጣን የሚያዘው በሕዝብ ነፃ፣ ፍትሃዊ እና ተአማኒነት ባለው ምርጫ መሆን እንዳለበት ያስታውሱት አቶ ደስታ፤ ሕገመንግስቱን የሚቃረን አዋጅ ሕግም ሆነ መመሪያ እንዲሁም የየትኛውም የመንግስት ኃላፊ ውሳኔ ተቀባይነት የለውም ብለዋል፡፡ ስለዚህ መንግስትም ሆነ ማንኛውም አካል በሕግ እና በሕገመንግስት በተሰጠው ስልጣን እና ኃላፊነት ውስጥ መንቀሳቀስ ይጠበቅበታል ብለዋል፡፡

አቶ ጀማል በበኩላቸው፤ በኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም እንዳይረጋገጥ በተለያዩ አካባቢዎች ግጭቶች ይነሳሉ፡፡ ስለዚህ ይህንን መሠረታዊ ችግር ለማጥፋት በሃይማኖት ተቋማትም ሆነ በትምህርት ቤት ስለ አብሮ መኖር ማስተማር በጣም ወሳኝ ነው ብለዋል፡፡

አቶ ጀማል እንዳብራሩት፤ ሰዎች በአብዛኛው ወደ ግጭት የሚገቡበት ከላይ እንደጠቀሱት መንስኤው መሃይምነት ወይም ብዙ አላዋቂዎች በመኖራቸው ነው። በሌላ በኩል ስልጣን ፈላጊዎች ደግሞ አላዋቂዎችን ስለሚጠቀሙባቸው ነው፡፡ ስለዚህ ሁለቱንም ለመከላከል መጀመሪያ በዕውቀት ላይ በጣም ሰፊ ሥራ ሊሠራ ይገባል፡፡ የትምህርት ዘርፉ ላይ ያለውን ካሪኩለም በደንብ መፈተሽ ወሳኝ ነው፡፡ ግጭትን የሚያስነሱ እና የሚያባብሱ ጉዳዮች በተለይም ታሪክን፣ የሰዎችን መስተጋብር እና ባህልን የመሳሰሉት የሚታዩበትን መነፅር በደንብ የሚያስተካክል አካሔድን ካሪኩለሙ መያዙን በደንብ ማጥናት ያስፈልጋል፡፡ ካሪኩለሙ ተደራሽነቱ ከተማ ላይ ብቻ ያንዣበበ መሆን የለበትም፡፡ ገጠሩንም ማካተት ይገባዋል ብለዋል፡፡

‹‹ትምህርት ቤት የማይሄዱ የሕብረተሰብ ክፍሎች በውድም ሆነ በግድ እንዴት ወደ ትምህርት ማስገባት ይቻላል? የሚለው ላይ መንግስትም ሕብረተሰቡም ሊሰራበት ይገባል፡፡›› የሚሉት አቶ ጀማል፤ ዕውቀቱ የሚዳረስበትን አካሔድ በተመለከተ በእርግጥ አንዳንዴ ውስንነት ይኖራል፡፡ በቅርብ ርቀት ትምህርት ቤት መገንባት ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ነገር ግን የኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ ኖሮ በምንም መልኩ ትምህርት የማያገኝ የሕብረተሰብ ክፍል ሊኖር አይገባም የሚል ትልቅ መነሳሳት እና ንቅናቄ በመፍጠር ዕውቀት ላይ በመሥራት የነገዋን ኢትዮጵያን ሰላም የሰፈነባት ማድረግ ይቻላል ብለዋል፡፡

በጣም ጥልቅ የሆነ የትምህርት ሒደት አንድ ልጅ በሕፃንነቱ በደንብ የሚጋትበትን እና የሚሠራበትን ሒደት በደንብ ሊታሰብበት ይገባል ይላሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ትልልቆች ምሳሌ በመሆናቸው አንዳንድ ጊዜ ትልልቆችንም በተለያዩ ሁኔታዎች ማሰልጠን እና ማስተማር የሚቻልባቸው ሁኔታዎች አሉ፡፡ ስለዚህ ወረዳ እና ዞን የሚባሉ መዋቅሮች ስለ ሰላም ሕብረተሰቡን ተደራሽ የሚያደርጉ አስተምህሮቶች ለትላልቆችም ቢሆን በሃይማኖት አባቶች በኩል ሊሰጥ ይችላል ብለዋል፡፡

መንግስትም ራሱ የተለየ አጀንዳ ሲኖረው ገበሬውንም ሁሉንም ሰብስቦ ፕሮፖጋንዳ እንደሚያስተጋባው ሁሉ የተለያዩ ትንንሽ ስልጠናዎችን የሚሰጡ አካሎችን በማዘጋጀት ሳምንታዊ ወይም ወርሃዊ ፕሮግራሞችን በማሰናዳት፤ የግጭት አፈታት ሂደት ላይ እና ግጭቶች እንዳይነሱ እንዴት መከላከል እንደሚቻል የሚያስተምሩ ትምህርቶች ሕብረተሰቡ የሚያገኝበትን ሁኔታ መፍጠር ይገባል ብለዋል፡፡

ትልልቅ ሰዎችም ከማንበብ እና ከዕውቀት ጋር ያሉበትን ሂደት መፈተሽ በጣም ወሳኝ ነው፡፡ እዚህ ላይ ያለውን ክፍተት ለመሙላት በእውቀት ላይ የሚሰሩት ሥራዎች በመሠረተ ትምህርት ላይ እንደተሠራው ሁሉ ትልልቅ ሰዎችን የማስተማር፤ ከአካዳሚው ውጪ ያሉ ሳምንታዊ ወይም ወርሃዊ ቋሚ ስልጠናዎች የማስኬድ፤ እውቀትን ተደራሽ ከማድረግ እና ግጭትን ከመፍታት አንፃር የሚሠሩ ሥራዎችን ማፋጠን በተለይ በገጠራማው አካባቢ የሚሰጡትን አስተምህሮቶች እና የተለያዩ ነገሮች በተለይ በመንግስት በኩል የሚሰጡትን አስተምህሮቶች ሕዝቡ እንዲያውቅ እና በትክክለኛው መንገድ እንዲያገኝ መጣር የግድ ነው ብለዋል፡፡

ብዙ ጊዜ በአገሪቱ ያሉ ግጭቶችም ሆኑ ጦርነቶች በትክክል መሳሪያ አንግቦ ጥቃት ሊያደርስ በሚችል መልኩ የሚነሱት ከገጠራማው አካባቢ ነው፡፡ ምናልባት የከተማው አካባቢ ከወሬ የዘለለ ብዙ ነገር ላያመጣ ይችላል፡፡ ስለዚህ በገጠሩ አካባቢ ላይ ከአካዳሚኩ ባሻገር መንግስት ራሱ የሚያደራጀው አካል ወይም ግጭትን ማስቀረት ላይ የሚሰሩ የሲቪክ ማኅበራት በጎ ፍቃደኞች በእነዚህ አካባቢዎች ላይ እየተሰማሩ ሕብረተሰቡን የማንቃት እና የማስተማር ሥራ መስራት ይገባቸዋል ብለዋል፡፡

እንደ አቶ ጀማል ገለፃ፤ ሰዎች በተለያዩ የሃይማኖት ጎራ ውስጥ የሚኖሩ በመሆናቸው አንዳንዴ ሃይማኖቶች የግጭቶች መንስኤዎች ይሆናሉ፡፡ አንዱ የሌላው ሃይማኖት ተከታይን የመጥላት ስብከት ስለሚኖር በክርስትናው ዓለም በሲኖዶሱ በእስልምናው ዓለም ደግሞ በዕስልምና ጉዳዮች ምክር ቤት ጥላ ስር የሚገቡበትን አካሔድ እና የአስተምሮታቸው ሒደት በደንብ በእውቀት የተቃኘ ነው አይደለም የሚለውን የሚገመግም አካሔድ ያስፈልጋል። በቤተክርስቲያንም ሆነ በመስጂድ እንዲሁም በተለያዩ የአምልኮት ቦታዎች ላይ የሚሰጡትን ትምህርቶች በሰላማዊነት መልክ መቃኘት እና ከሚያስተምሩት ጋር ልዩ ስብሰባ በማድረግ በሰላም ላይ ያላቸውን እይታ ቅርፅ ማስያዝ ይገባል፡፡

የሃይማኖት አስተምህሮቶች ሂደት አንዳንዴ ከውጪ ተቀብተው መጥተው ለጠብ መነሳሻ እና ማባባሻ የሚሆኑበት እንዲሁም የሌሎች ፖለቲካ ውስጣቸው ተቀላቀለው የሚሄዱበት ሁኔታ መኖሩን በማስታወስ፤ በደንብ ለማየት የሃይማኖት አባቶች በጋራ ሆነው በተለይም በወሳኝ እና በጋራ ጉዳዮች ላይ በመግባባት በደንብ መስመር አስይዘው ወጥ በሆነ መልኩ ሊሠሩ ይገባል ብለው እንደሚያምኑ ተናግረዋል፡፡

ሌላው በአቶ ጀማል የተነሳው እንደ አቶ ደስታ ሁሉ ሕግ ማስከበር የግድ ነው የሚል ነው፡፡ ብዙ ጊዜ እውቀት ኖሮትም ሆነ ሳይኖረው ጥፋት እና የሕግ ጥሰትን የሚፈፅም ኃይል ይኖራል፡፡ የትም አገር ከዕውቀት እና ከአስተምሮት ውጪ የሆኑ አካሄዶችን ለማረቅ ሕግን ማስከበር ያስፈልጋል፡፡ ለምሳሌ ሰው የመንጃ ፍቃድ ሲያወጣ ሕጉን ጠብቆ እንዲያወጣ ይደረጋል፡፡ ሕጉ የማይጠብቅ ከሆነ እና በሙስና መንጃ ፍቃዱ ከተገኘ የመኪና አደጋ ይበዛል፡፡ ነገር ግን በጠበቀ ሕግ መንጃ ፍቃድ ከወጣ በኋላ፤ ዕውቀቱ ኖሯቸው መንገድ ላይ በማሽከርከር ሂደት ሥርዓቱን ጠብቀው የማያሽከረክሩትን በየትኛውም ዓለም በካሜራ ወይም በተለያዩ ፖሊሶች ተይዘው ጥፋታቸውን የሚመጥን ቅጣት ይቀጣሉ፤ ይህ የግድ ነው ያለበለዚያ ተመጣጣኝ ጥቃት ካልተሰጠ ሰዎች ለጥፋት ይነሳሳሉ፡፡ ስለዚህ ሕግ የማስከበር ጉዳይም ችላ የሚባል አለመሆኑን አስረድተዋል፡፡

እንደ ሁለቱም ሃሳብ ሰጪዎች ገለፃ፤ የነገዋ ኢትዮጵያ ሰላማዊ እንድትሆን ዕውቀትን ማስፋት እና ሕግን ማስከበር በተመለከተ መንግስት እና ሕዝቡ በትኩረት መሥራት እንዳለባቸው አመላክተዋል፡፡ በእነዚህ ላይ በአግባቡ ከተሠራ በቀጣይ ዓመትም ሆነ ለዘለቄታው ሰላም የማይሰፍንበት ምክንያት እንደሌለም አመላክተዋል፡፡

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ሴቶችና አዲስ ዓመት

**ሰሚራ በርሀ**



ሲስተር ውብታዬ ገዳ፣



ዲዛይነር ሜሪያም ሰብስ፤

ዲዛይነር ሜሪያም ሰብለ ትባላለች፡፡ በአሁን ሰዓት « ሜሪያም አስቴቲክስ » የተሰኘ ሀሳቤንና ምልከታዬን ይገልጹልኛል ያለቻቸውን ዲዛይኖቿን በሀገር ባህል ልብሶች ላይ በማሳረፍ ስራዎቿን ለገበያ ታቀርባለች።። ሰዎችን መሳብ እና ደንበኞቸ ማፍራትም ችላለች፡፡

በስራው ላይ አምስት ዓመት የቆየችው ሜሪያም ወደዚህ ስራ ከመግባቷ አስቀድሞ ትምህርቷን ያጠናቀቀችው በሆቴል ማኔጅመንት ነበር፡፡ በስራው ውስጥም ለስድስት ዓመት ያክል ቆይታለች፤ ታዲያ ወደዚህ የፋሽን ዲዛይን ስራ እንድትገባ ያደረጋት አጋጣሚ የተፈጠረው የኮቪድ ወረርሽኝ የዓለም አቀፍ ስጋት መሆኑ ይፋ ተደርጎ እንቅስቃሴዎች በተገደቡበት ወቅት ሜሪያም የራሷን ስራ ለመስራት ፍላጎቷን በመመርመር የራሷን የተለያዩ ጥናቶች ማድረግ ጀመረች።

ለተፈጥሮ ቅርበት ያላት ሜሪያም ይህን የፋሽን ኢንዱስትሪ ጥሩ ሆኖ አገኘችው፡፡ በዚህም ከመደበኛ ስራዋ ጎን ለጎን የፋሽን ስራው ላይ ትኩረት ማድረግ እና ቢዝነሱን በሁለት እግሩ እንዲቆም ለማድረግ መስራቷን ቀጠለች፡፡ « መደበኛ የሙሉ ቀን ስራ ኖሮኝ ከዛ ደግሞ የራስን ቢዝነስ ማስኬድ በጣም ከባድ ነበር።» የምትለው ሜሪያም የራሷን ስራ ከመጀመሯ በፊት ተቀጥራ ለስድስት ዓመት የሰራች ሲሆን ከዚህ ጊዜ በኋላ የቀድሞ ስራዋን ትታ ሙሉ ለሙሉ ወደ ራሷ ስራ ለማተኮር ለመወሰን የተቸገረችበት ጊዜም ነበር፡፡

«በፊት በምሰራበት ቦታ የሚከፈለኝ ደሞዝ፣ የምሰራበት ክፍል ጥሩ ስለነበር ስራዬን ሙሉ ለሙሉ ለማቆም እርግጠኛ አልነበርኩም፡፡ » ስትል ሁኔታውን ታስታውሳለች፡፡ ሜሪያም የራሷን ስራ ከጀመረች አራት ዓመት ያክል ጊዜ ቆይታለች፡፡ « የ2016 ዓ.ም ራሴን የፈተሸኩበት አቅሜን ያየሁበት እና ብዙ ነገር የተማርኩበት ነው እና ማንኛውም ሰው የራሱን ስራ ለመጀመር ሲያስብ ሙሉ ለሙሉ እርግጠኛ መሆን አይጠበቅበትም አንድ ትልቅ ነገር ለመጀመር ስናስብ ደግሞ የፍርሀት ስሜት ማስተናገድ የተለመደ በመሆኑ ወደኋላ ሊያስቀረን አይገባም፡፡ » ትላለች፡፡

ሜሪያም ከዚህ ቀደም የምትሰራበት የራሷ ሱቅ ከመሀል ከተማ ራቅ ያለ በመሆኑ በ2016 ዓ.ም ውስጥ አንዱ እቅዷ ይህንን ሱቋን ወደ ሌላ አማካኝ ወደሆነ ቦታ መጥቶ መክፈት ነበር፡፡ ይህንንም አሳክታዋለች። በዚህም እቅዷ የነበረውን ደንበኞችን ማብዛት ሽያጮቿን መጨመር እና ስራዋን የምታስተዋውቅበትን የማህበራዊ ገጽ ላይ ያላትን ተሳትፎ ማሳደግ በዚህ ዓመት ያሳካቻቸው ናቸው፡፡ ሜሪያም ከስራዋ ባሻገር የተለያዩ ቦታዎችን እየተዘዋወሩ መጎብኘት አብዝታ የምትወደው በመሆኑ በአሁን ሰዓት በግል ስራዋ ላይ በማተኮሯ ብዙም ጉብኝት ማድረግ አልቻለችም፡፡

ሜሪያም እንደ ግለሰብም ሆነ እንደማኅበረሰብ የተሻለ ቦታ ለመድረስ እና የተሻሻለ አስተሳሰብ ያለው ለመሆን መማር ምርጫ የሌለው ጉዳይ መሆኑን ትጠቅሳለች፡፡ በአሁን ሰዓት ከመደበኛ የትምህርት ስርዓት ባሻገር ሰዎች ፍላጎታቸው ያደረበትን ዘርፍ በመምረጥ እና በአጭር ጊዜ የሚጠናቀቁ ትምህርቶችን በመውሰድ በራሳቸው ስራ ላይ ተሰማርተው ገንዘብ መስራት ጀምረዋል፡፡ ሜሪያም በዚህ ዙርያ ከብዙ ወጣቶች ጥያቄዎች ይደርሷታል፡፡ « ብዙዎች ሳይማሩ ገንዘብ መስራትን እንደትልቅ ነገር በማየት ትምህርትቤት ገብቶ መማር ግዴታ ነው ወይ እያሉ ይጠይቁኛል፡፡ » ነገር ግን እንደ ሀገር ለምንሰማቸው አንዳንድ መልካም ያልሆኑ ዜናዎች በሴቶች ላይም ሆነ በሰዎች ላይ ለሚደርሱ ጥቃቶች ምክንያቱ አለመማር ነው፡፡ መማር ማለት ደግሞ ማገናዘብ በመሆኑ ትምህርት አስፈላጊ መሆኑን ትጠቅሳለች፡፡ « ሴቶች ራሳቸውን በኢኮኖሚም ሆነ በአመለካከት ልቀው ለመገኘት መማር ትልቁ መሳርያቸው ነው፡፡ » ትላለች፡፡

ሜሪያም በ2017 ዓ.ም የራሷን ቢዝነስ ማስፋፋት እና ትልቅ ደረጃ ላይ ማድረስ፤ ራሷን በእውቀት ማሳደግ እና የተለያዩ ቦታዎችን መጎብኘት በእቅዷ ውስጥ ያለ ነው፡፡

ሌላኛዋ በስራ ላይ የምትገኘው እንስት አይናለም እሸቱ ትባላለች፡፡ አይናለም ባለትዳር እና የሁለት ልጆች እናት ስትሆን ብዙውን ግዜ ወንዶች ተሰማርተውበት በሚገኘው በሊስትሮ ስራ ላይ ተሰማርታ ትገኛለች ፡፡ « ወደ ስራው ስገባ የወንድ የሴት ስራ ነው ብዬ በፍጹም አላሰብኩም፡፡ » የምትለው አይናለም በዚህ ስራ ላይ አንድ ዓመት ያክል ጊዜ በአራት ኪሎ አካባቢ በመስራት ላይ ትገኛለች፡፡

አይናለም ትውልዷ በሰላሌ ሲሆን ወደ አዲስ አበባ ስትመጣ በሰው ቤት ውስጥ ተቀጥራ ስትሰራ ቆይታለች፡፡ ለአምስት ዓመታት ያህል ሰው ቤት ስትሰራ ከቆየች በኋላ የራሷን ትዳር መሰረተች፡፡ ስራዋንም ትታ የቤት እመቤት ሆና ለተወሰኑ ዓመታት ከቆየች በኋላ ባለቤቷን ለማገዝ ወስና ወደ ሊስትሮ ስራ ገባች፡፡ እሷ ጋር ጫማቸውን ለማስጠረግ የሚመጡ ሰዎችም እንደሚያደንቋትና እንደሚያበረታቷት ትገልጻለች፡፡

አይናለም የሁለት ልጆች እናት ስትሆን የመጀመርያ ልጇ የአምስት ዓመት፤ ሁለተኛ ልጇ ደግሞ የሶስት ዓመት ሲሆኑ ልጇን ለማሳደግ እና ትምህርት ቤት ለመላክ ይህ የሊስትሮ ስራ ጥሩ ሆኖ አግኝታዋለች ፤ የ2017 ዓ.ም እቅዷም ልጆቼን ማሳደግ ነው ስትል ትገልጻለች፡፡ አይናለም የሊስትሮ ስራዋን ዘወትር የምታከናውነው በአራት ኪሎ አካባቢ ሲሆን መኖርያዋ ግን በእንጦጦ ማርያም ሰፈር ነው፡፡ ታዲያ ጠዋት የልጆቿን ምግብ አዘጋጅታ ከ12 ሰዓት በኋላ በስራዋ ላይ ትገኛለች ፤ ማታም እንዲሁ እንደምታስተናግደው ሰው በማየት ስራዋን እስከ ምሽት 12 ሰዓት እስከ አንድ ሰዓት በመስራት ከምሽቱ ሁለት ሰዓት ወደቤቷ ታመራለች፡፡ አይናለም በስራ ቀኗ በከተማችን እየተከናወነ የሚገኘው የኮሪደር ልማት እና ቦታው ላይ ደንብ ከቦታቸው የሚያስነሷቸውን ተቋቁማ ስራዋን ሰርታ እና የምታገኘውን ገንዘብ ቆጥባ የቤት ኪራይ፣ የታክሲ ወጪ እና የልጆቿን ትምህርት ቤት ትሸፍናለች፤ በዚህም በጣም ደስተኛ ናት ፡፡

አይናለም የራሷን የንግድ ስራ መጀመር የወደፊት እቅዷ እንደሆነ ገልጻ ነገር ግን በራሴ አቅም ሰርቼ መለወጥ ስለምችል የሰዎችን እርዳታ አያሻኝም በማለት ጠንክሮ መስራት የሚያስገኘውን ለውጥ እንደምትተማንበት ትገልጻለች፡፡ በ2017 ዓ.ም በዚሁ ስራዋ በመቀጠል ሌሎች የተሻሉ ስራዎችን የመስራት እና ለልጆቿ የተሻለ ሕይወትን መስጠት የአይናለም እቅዷ ነው፡፡

በጤና ተቋማት ውስጥ ሴቶች ከሚመረጡበት የስራ ሙያ እና እምብዛም ትኩረት የማይሰጠው ነገር ግን ወደጤና ተቋም የሚመጡ ታካሚዎችን በመንከባከብ እና ቅርባቸው በመሆን ብዙ ዋጋ የሚከፈልበት ሙያ ነው የነርሲንግ ሙያ፡፡ ሲስተር ውብታዬ ገዳ ይባላሉ በነርሲንግ ሙያ የመጀመርያ ዲግሪያቸውን የያዙ ሲሆን ሲኒየር ነርስ ሆነው በማገልገል 10 ዓመትን አገባደው ወደ አስራ አንደኛው እየተጠጉ ነው፡፡ « የነርሲንግ ሙያ መሰጠትን እና ከልብ የሆነ ፍላጎትን ይጠይቃል፡፡ እርዳታ ፈልጎ ወደ ሆስፒታል የሚመጣን ሰው ለመርዳት ቅንነት ትዕግስት ያስፈልጋል፡፡ እንደዛ ካልሆነ በስራው ላይ ለመቆየት በጣም ይከብዳል፡፡ » በዚህም አንዳንድ ጊዜ ሰዎች በጤና ተቋማት ላይ ቅሬታ ሲያቀርቡ ሲሰማ ቦታው ላይ የሚሰሩት ሰዎች ሙያውን ይወዱታል ወይ የሚለውን መጠየቅ ያስፈልጋል ትላለች፡፡ በዚህም ሴቶች የተሻሉ ሲሆን በስራ ቆይታዋ ነፍሰጡር ሆነው፤ ከወለዱ በኋላም በዚሁ ስራ ላይ ሰዎችን በማገልገል ያሳልፋሉ፡፡

ሲስተር ውብታዬ የአንድ ልጅ እናት ስትሆን የምትሰራው በጃንሜዳ ጤናጣቢያ ላይ ለአስር ዓመት ያክል ቆይታለች አሁንም በስራው ላይ ትገኛለች፤ በስራዋም ደስተኛ መሆኗን ትገልጻለች ፡፡ እንደ የጤና ባለሙያ አምሽቶ መስራት፤ በጠዋት መግባት እና አዳሪ ሆነው በተቋሙ ውስጥ ማሳለፍ የተለመደ ነው። ታዲያ ይህ ስራ ለአንዷት ቤተሰብን ለምትመራ ሴት አይከብድም ወይ ብለን ላቀረብንላት ጥያቄ « በቤት ውስጥ ያለ የትዳር አጋርም ሆነ አብሮ የሚኖር ሰው አስቀድሞ መረዳት እና ማገዝ ይገባዋል፡፡ ምክንያቱም ድንገተኛ በሆኑ አደጋዎች አልያም እርዳታ በሚያሻቸው ጉዳዮች ላይ ከቤታቸው ተጠርቶ መሄድ ስላለ ሙያውን መረዳት ያስፈልጋል» ትላለች፡፡ ሲስተር ውብታዬ መኖርያዋ ለምትሰራበት ቦታ ቅርብ በመሆኑ የሚኖራትን የስራ ጫና በእጅጉ እንደሚቀንስላት ትገልጻለች፡፡

ሴቶች አንድ ጊዜ ወደ ትዳር ከገቡ እና የራሳቸውን ሕይወት ከመሰረቱ በኋላ በትምህርት ራሳቸውን ማሳገድ ይልቅ ምናልባት ለቤተሰባቸው ቅድሚያ በመስጠት ትምህርታቸውን ላይቀጥሉ ይችላሉ ወይዘሮ ውብታዬ ለዚህ የራሷን እና የስራ ባልደረቦቿን ጥንካሬ ያስታውሳሉ፡፡ « እኔ ስራ እንደጀመርኩ ነበር ዲግሪዬን የተማርኩት ነገር ግን በምሰራበት ቦታ የነበሩ ሴቶች ትዳር መስርተው ልጆች ኖሯቸው ነፍሰጡርም ሆነው ጭምር የማታ እና የርቀት እየተማሩ ትምህርታቸው ይማራሉ፤ በጣም የሚገርመው ደግሞ የሚያመጡት ውጤትም የተሻለ ነበር፡፡ » በማለት የሴቶቹን ጥንካሬ ትገልጻለች፡፡ ይህ ደግሞ ሴቶች ከልባቸው ከፈለጉ ማሳካት እንደሚችሉ እና የተሰጣቸውን ኃላፊነት በብቃት መወጣት እንደሚችሉ ማሳያ ነው ትላለች፡፡

ሲስተር ውብታዬ 2016 በስራዋ ጥሩ የሚባል ዓመትን እንዳሳላፈች ገልጻ ቀጣዩን የ2017 ዓመት ለመላው ኢትዮጵያውያን፣ ለጃንሜዳ ጤና ጣቢያ ሰራተኞች እንዲሁም ለቤተሰቦቿ መልካም አዲስ ዓመትን እንዲሁም እንደ ሀገር መልካም ነገር የምንሰማበት እና የስኬት ዓመት እንዲሆን ተመኝታለች፡፡

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

ግርማ መንግሥቴ

**ታሪክ ራሱን ሲደግም እንመለከትና እንታዘብ ዘንድ፣ ያኔ ምን ሆነ ዛሬስ ምን እየሆነና እየተደረገ እንደሆነ እንመለከት ዘንድ አዲስ ዘመን የማይተካ ድርሻውን ሲወጣ መመልከት እንግዳ ደራሽ አይ ደለም። ልክ እንደ እስከዛሬው ሁሉ፣ ዛሬም የሚለን አለና (በተለይ የግብፅን በሶማሊያ መገኘት) እንደሚከተለው ይነበባል።**

### የፖለቲካ ድብብቆሽ ጨዋታ

ኢጣሊያኖች በብዙ ሚሊያርድ የሚቆጠር ገንዘብ ለሶማሊያ አጠፉን የሚሉት የዚህ ገንዘብ መጥፋት የሚመሰክረው አሁን አይደለም። ለሶማሌ ብልፅግና፣ ለሶማሌ ደህንነት የተባለው ይህ ገንዘብ የሶማሌን ጠባይ፣ የሶማሌን ባህል የሶማሌን እውነተኛና ዘላቂ ጥቅም ለማጥፋት የተሰነዘረው ረቂቅ አመራር፣ ከሀገሩ ላይ ጨርሶ የተወገደ ጊዜ ብቻ ነው።

በእውነተኛው መንገድ ገንዘቡ ተገቢ ቦታውን ይዞ ጠፋ ለማለት የሚቻለው ሶማሌዎች ነፃነታቸውን ተረክበው የአስተዳደራቸው ባለቤት በመሆን የውጭ ፖለቲካቸውንና የውስጥ ፖለቲካቸውን አስማምተው የሚራመዱበትን ትክክለኛ መስመር ሲይዙ ነው እንጂ፣ የመልካም ጉርብትናንና የወዳጅ ፍቅርን አጥፍተው ሰላምን ለሚያደፈርሱበት ሁኔታ፣ ወጣ የተባለው ገንዘብ ለጥፋት የወጣ መሆኑን የህሊና አስተያየት ሊስተው አይችልም።

ጠቅላላውንም አስተያየት ብንወስድ፣ እውነት ለሶማሌ ታስቦ ቢሆን፣ እንደ ከንቱ ህልም በሚቆጠር ሃሳብ ውስጥ ሶማሌዎች ገብተው እንዲዋኙ ባልተደረገም ነበር። ኢትዮጵያ ይህንኑ ሁኔታ አርቆ በማሰብና በመመልከት ቀድሞውንም ሶማሊያ በማንም ሞግዚትነት ስር እንዳትደዳር የተቃወመችው ይኸው አሁን በሶማሌ የሚሠራባት ድርጊት እንዳይደርስባት ነበር።

አሁንም ቢሆን ለሶማሌ ነፃነት የኢትዮጵያን ያህል የሚያስብላት እንደሌለ በጥልቅ ሊገነዘቡት የሚችሉት፣ ሶማሌዎች የራሳቸው ጉዳይ ባለቤት የመሆንን እድል ሲያገኙ ብቻ መሆኑ ጥርጥር የሌለበት ስለሆነ፤ በዚህ የተገለጡት ሃሳቦች ምን ያህል መሠረትነት ያላቸው መሆናቸውን በዚያን ጊዜ የበለጠ ይረጋገጣሉ።

ሶማሌዎች ከኢትዮጵያ እንዲጣሉ በመገፋፋት በሚደረገው የፖለቲካ ድብብቆሽ ጨዋታ ውስጥ በመግባታቸው፣ ከጉዳት በቀር አንዳች ጥቅም እንዳላገኙ ለመረዳት እስካሁን የደረሰባቸው በቂ ትምህርት ሊሆናቸው ስለሚችል፤ ለራሳቸው ሲሉ ሶማሌዎች ወደ ፊት በጣም መጠንቀቅ እንዳለባቸው ይዘነጉታል ብለን አንጠራጠርም።

**(አሳምነው ገብረ ወልድ፣ አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 1 ቀን 1951 ዓ•ም)**

### አዲስ መጽሐፍ

ግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ ኃይለሥላሴ፣ ለሀገራቸው ልማት፣ ለሕዝባቸው እድገት ሲሉ ያለ እረፍት በሀገር ውስጥም ሆነ፣ በውጭ ሀገር ያለ ማቋረጥ የሚያደርጉት ጉብኝት ከፍ ያለ ጥቅም የሚገኝበት መሆኑ አይዘነጋም።

በዚህም መሠረት ከግንቦት 1 ቀን እስከ ግንቦት 18 ቀን 1951 ዓ•ም ድረስ፣ የጎጃምን፣ እንዲሁም የቤገምድርንና የሰሜንን ጠቅላይ ግዛቶች ጎብኝተዋል። በጉብኝታቸውም ጊዜ የመጀመሪያውን የዓባይን የሃይድሮ ኤሌክትሪክ መሠረት፣ የጨርቃጨርቅ ፋብሪካ፣ ጎጃምና ቤገምድርን የሚያገናኝ አዲስ ድልድይ መስርተዋል። በነዚህም በ 2 ጠቅላይ ግዛቶች ሕዝቦቻቸው መካከል በሰነበቱባቸው እለታት ውስጥ ግርማዊነታቸው ለሕዝባቸው ያደረጉት ሰፊ ልግስና ሕዝባቸው ለግርማዊነታቸው ያደረገው ልባዊ አቀባበል ለትውልድ እንዲወራረስ 199 ገጽ የሆነ ከዚሁ 42ቱ ልዩ ልዩ ሥዕሎች ያሉበት ፣ የዓባይ ውሃ ልማት መጀመሪያ መሠረት፣ የሚል መጽሐፍ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ተዘጋጅቶ በመልካም አቀራረብ በንግድ ማተሚያ ቤት ታትሞ ወጥቷል። መጻሕፍት ወዳጆችና ታሪክ አጠናቃሪዎች የሆኑ ሁሉ መጽሐፉን እየገዙ ለመጠቀም እንዲችሉ ያሳስባል።

**(አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 21 ቀን 1951 ዓ•ም)**

### ለወላጆች ምክር

አደጋ በህፃኒቱ ላይ ሊደርስ የቻለበት ምክንያት ወላጆች ለልጆቻቸው ገና በቡቃያነታቸው በሚገባ አስደተዳደግ ሳይመሯቸው በመቅረት ካደጉ በኋላ በዱላ ነርተን ልብ እናስገኝላቸዋለን በማለት ሁኔታ የሚፈፀም መሆኑን ይህ አደጋ ደርሶባቸው የሚመጡትን ህፃናት በምንጠይቅበት ጊዜ አረጋግጠው ያስረዱናል።

የሚገባ አይደለም፤ ዱላ ሲበዛ ያደነዝዛል እንጂ ልብ አይሰጥም። በአንዳንዶቹ አንደበት ሲነገር እንደምንሰማው የዱላ ክፋቱ ለሸክላ እንጂ ለሌላ ሁሉ ልብ ይሰጣል በማለት ሲተርቱ ስለምንሰማ ጠባያቸውን እንዲያርሙ ይህ ሁኔታ ባጋጠመን ጊዜ መክረን ለማለፍ አልቦዘንም ነበር።

አሁን ግን እላይ እንዳተትነው ይህ አደጋ የሚደርስበት ከዚሁ ከአንዱ ክፍል ሲሆን፣ ጥፋተኞቹ ወላጆቹ ይሁኑ ወይንም ህፃኖቹ ለመፍረድ አስቸጋሪ ስለሆነ፤ የህፃኖቹን ፋንታ አልፈን ስለ ጥፋተኛነቱ ወላጆቻቸውን ሳንመለከት አልቀረንምና ህፃንን በዱላ ቀጥቅጬ ልብ እሰጠዋለሁ ማለት የውቅያኖስን ውሃ ቀድቼ እጨርሳለሁ ከማለት ጋር እኩል የሚቆጠር በመሆኑ፤ በመጀመሪያ በቡቃያው አኮታኮትን ማሳመር ስለሚያሻ ለህፃናቶችም በሚገባ ቢታሰብላቸው የተሻለ ነው።

**(አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 12 ቀን 1951 ዓ•ም)**

### የኢትዮጵያ እግር ኳስ ቡድን ውጤት

የኢትዮጵያ ናሲዎናል ቡድን ከሶቪየት ናሲዎናል ኦሎምፒክ ቡድን ጋር ባደረገው ግጥሚያ 12 ለ 3 ተለያይተዋል። ሁለተኛው ግጥሚያ ማክሰኞ ሀምሌ 7 ቀን ዜኒት ሌኒንግራድ ከሚባል ቡድን ጋር ተጋጥመው 2 ለ 1 ተለያይተዋል። ዜኒት ባለፈው ወር ረንስ የተባለውን 8 የፈረንሳይ ናሲዎናል ተጫዋቾች ያሉበትን ቡድን ባሁኑ አመት ለአውሮፓ ሻምፒዮና ፍፃሜ ተካፋይ የነበረውን 3 ለ0 አሸንፎታል።

የጨዋታው ሀተታ እንደደረሰን በሰፊው እናትታለን።

**(ፍቅሩ ኪዳኔ፣ አዲስ ዘመን፣ ሐምሌ 10 ቀን 1951 ዓ•ም)**

### በወ ወ ክ ማ የሚደረግ ንግግር

ነሐሴ 9 ቀን 1951 ዓ፨ም ከምሽቱ 1 ሰአት ጀምሮ አቶ ዮሀንስ ወልደ ገሪማ በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት የሕዝብ ጤና ጥበቃና የሕዝብ አገልግሎት ዲሬክተር ፣የሕዝብ አገልግሎት፣ በሚል አርዕስት በወጣቶች ወንዶች ክርስቲያናዊ ማኅበር አዳራሽ ንግግር ስለሚያደርጉ ማንኛውም ሰው ንግግሩን ሊያዳምጥ ይችላል።

**(አዲስ ዘመን፣ ነሀሴ 8 ቀን 1951 ዓ•ም)**

# ዓለም አቀፍ

## በፊሊፒንስ እና በአሜሪካ ሕጻናትን ለወሲብ ንግድ ሲያዘዋውር ነበር የተባለ ፓስተር በቁጥጥር ስር ዋለ

በጋዜጣው ሪፖርተር

**አዲስ አበባ፡-** ሕጻናትን ለወሲብ ንግድ በማዘዋወር በፊሊፒንስ እና በአሜሪካ በጥብቅ ሲፈለግ የነበረው ተፅዕኖ ፈጣሪው ፓስተር በቁጥጥር ስር ዋለ።

ፖሊስ እራሱን 'የእግዚአብሔር ልጅ' እያለ የሚገልጸውን ፊሊፒንሳዊውን አፖሎ ኩይቦሎይን በቁጥጥር ሥር ለማዋል የሚሰብክበትን ቤተክርስቲያን ለሁለት ሳምንት ያህል ከቦ ቆይቷል።

በዚህም ምክንያት በሺዎች በሚቆጠሩ ተከታዮቹ እና በፖሊስ መካከል ውጥረት ተፈጥሮ የነበረ ሲሆን አንድ የቤተክርስቲያኑ አባል በልብ ድካም ሕይወቱ ሊያልፍ ችሏል።

ሰባት ሚሊዮን ተከታዮች እንዳሉት የሚገልጸው ኩይቦሎይ የቀረቡበትን ሁሉንም ክሶች አጣጥሏል።

ኩይቦሎይን ሕጻናትን በወሲብ ንግድ ዝውውር፣ በማጭበርበር እና ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብን በሕገ ወጥ መንገድ በማዘዋወር በአሜሪካ የፍትሕ መሥሪያ ቤት ክስ የቀረበበት እንደ አውሮፓውያኑ 2021 ነበር።

የአሜሪካ ፌዴራል ፖሊስ (ኤፍቢአይ) እንዳለው ፓስተሩ ልጃገረዶችን እና ሴቶች ለገንዘብ ማስገኛ ከፊሊፒንስ ወደ አሜሪካ አዘዋውሯል።

ከዚህም በተጨማሪ ሴት ረዳቶቹን ከእርሱ ጋር ወሲብ እንዲፈፅሙ መጠየቁን ኤፍቢአይ ገልጿል።

ይህ ሁሉ የሆነው ኩይቦሎይ የቀድሞው የፊሊፒንስ መሪ ሮድሪጎ ዱቴርቴ መንፈሳዊ አማካሪ መሆኑን ተከትሎ እውቅናው እየጨመረ በመጣበት ወቅት ነው።

ሆኖም እንደ አውሮፓውያኑ ሰኔ 2022 ዱቴርቴ ከሥልጣን መልቀቃቸውን ተከትሎ ፓስተሩ የነበረው ዝና ተለውጧል።

በቅርቡ የፊሊፒንስ ባለሥልጣናት በሕጻናት ጥቃት፣ ወሲባዊ ጥቃት እና በሕገ ወጥ የሰዎች ዝውውር ክስ ያቀረበቡበት ሲሆን እንዲታሰር የእስር ማዘዣ አውጥተውበት ነበር።

ኩቦሎይን ለመያዝ በሺዎች የሚቆጠሩ ፖሊሶች በዳቫኦ የሚገኘውን 30 ሔክታር ስፋት ያለውን ቤተክርስቲያኑን ለሁለት ሳምንት ያህል ከብበው ቆይተዋል።

ፖሊሶች ፓስተሩ ለሁለት ሳምንት ያህል ምድር ቤት ውስጥ ተደብቆ እንደነበር በደህንነት መሣሪያ መለየቱን አስታውቀዋል።



ቅጥር ጊቢው ውስጥ ቤተክርስቲያንና ትምህርት ቤትን ጨምሮ 40 ሕንጻዎች አሉት።

የኩይቦሎይ ጠበቃ እንዳሉት ፓስተሩን ለመያዝ ፖሊስ ለሁለት ሳምንት ያደረገው ከበባ ጊቢውን (ኬኢጂሲ) ወደ የፖሊስ ሰፈር ለውጦት ነበር በማለት በተፈጠረው ውጥረትም አንድ አማኝ እንዲሞቱ ምክንያት ሆኗል ብለዋል።

የብሔራዊ ፖሊስ ቃል አቀባይ ኮሎኔል ጂን ፋጃርዶ፣ እሑድ ዕለት ኩይቦሎይ በሰላም እጁን እንዲሰጥ የተሰጠውን የ24 ሰዓት ጊዜ ተከትሎ በሰላም እጁን መስጠቱን ተናግረዋል።

ሆኖም ጠበቃቸው እስራኤሊቶ ቶሬን ደንበኛቸው እጁን የሰጠው አላስፈላጊ ግጭትን ለማስቀረት እንደሆነ ገልጸዋል።

ኩይቦሎይ ከመታሰሩ በፊት 'ሰይጣን ሕጋዊ ሥራቸውን እየተፈታተነ' እንደሆነ ተናግሮ ነበር። በጉዳዩ ላይ ኤፍቢአይ እንዳይገባም ገልጾ ነበር።

የአሜሪካ ፍትሕ መሥሪያ ቤት ቀደም ሲል በሕጻናት የወሲብ ንግድ፣ በማጭበርበር እና በጅምላ የገንዘብ ዝውውር ወንጀል ኩይቦሎይ ላይ ክስ አቅርቦ የነበረ ሲሆን ዱቴርቴ ሥልጣናቸውን ለአሁኑ ፕሬዚዳንት ፈርዲናንድ ማርኮስ ጁኒየር ከማስረከባቸው ከጥቂት ወራት በፊት እንዲታሰር ይፈልግ ነበር። ሆኖም ባለሥልጣናት ፓስተሩን የመከታተል ሥራ የጀመሩት በማርኮስ የሥልጣን ዘመን ነበር ሲል ቢቢሲ ዘግቧል።

## በናይጄሪያ ነዳጅ ጫኝ ቦቴ ከሌላ መኪና ጋር ተጋጭቶ 48 ሰዎች ሞቱ

በጋዜጣው ሪፖርተር

በናይጄሪያ ማዕከላዊ ግዛት ኒጀር አንድ ነዳጅ ጫኝ ተሽከርካሪ ሰዎች እና የቁም እንስሳትን ከጫነ መኪና ጋር ተጋጭቶ ቢያንስ 48 ሰዎች መሞታቸው ተገለጸ።

በሁለቱ መኪኖች ግጭት የተነሳው ከባድ ቃጠሎ ለሰዎች እና እንስሳት ሞት ምክንያት መሆኑን የሀገሪቱ የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ኤጀንሲ አስታውቋል።

ኤጀንሲው ይህ አደጋ ያጋጠመው ትናንት ዕሁድ እንደነበር ገልጾ ሁለቱ ተሽከርካሪዎች ሲጋጩ ከፍተኛ ፍንዳታ ተከስቶ እንደነበር ጠቅሷል። በዚህም ሳቢያ ተሽከርካሪዎቹ ሙሉ በሙሉ መቃጠላቸውን አመልክቷል።

የናይጄሪያ የአደጋ ጊዜ አስተዳደር ኤጀንሲ ዳይሬክተር ጄነራል አቡዱላሂ ባባአራህ ክስተቱ ወዳጋጠመበት ሥፍራ የአደጋ መከላከል ሠራተኞች ቡድን እንደተላከ ተናግረዋል።

ሌሎች በርካታ ተሽከርካሪዎችም በአደጋው ምክንያት በተፈጠረው ፍንዳታ ጉዳት እንደደረሰባቸውም ተገልጿል። አደጋው ከተከሰተ ከጥቂት ደቂቃዎች በኋላ በማህበራዊ ሚዲያ የተለቀቁ ቪዲዮዎች የተጋጩት ሁለት ተሽከርካሪዎች ሙሉ በሙሉ ወድመው አስመልክተዋል። በተጨማሪም በእሳት ተቃጥለው የሞቱ እንስሳትም ይታያሉ።

ሮይተርስ ያነጋገረው አንድ የአደጋ ጊዜ ሠራተኛ ከባልደረቦቹ ጋር በመሆን የሞቱ ሰዎችን አስከሬን እያወጡ እንደሆነ ተናግሯል። ጨምሮ እስካሁን ያልወጡ የሞቱ እንስሳትን ከተሽከርካሪዎች የማውጣቱ ሥራ እንደቀጠለ ገልጿል።

የሞቱ ሰዎች በጅምላ መቃብር ውስጥ መቀበራቸውን የናይጄሪያ ብሔራዊ የቴሌቪዥን እና ሬዲዮ ጣቢያ ዘግቧል። በናይጄሪያ የኒጀር ገዢ ኡማር ባጎ በዚህ ክስተት ኀዘን እንደተሰማቸው ገልጸው በአደጋው ሰለባ ለሆኑ ሰዎች ቤተሰብ መጽናናትን ተመኝተዋል።

በናይጄሪያ በተለይም በመንገድ ችግር ምክንያት የነዳጅ ጫኝ ተሽከርካሪዎች ፍናዳታ እና የመኪና አደጋ በተደጋጋሚ የሚያጋጥሙ ችግሮች ናቸው።

የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን
Ethiopian Cooperative Commission
(ECC)

# ከኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን ጋር በመተባበር
በየሳምንቱ የሚታተም

## የአቅርቦት እጥረት እንዳይኖር ዝግጅት የተደረገበት አዲሱ ዓመት

በካሳሁን ገ/መድህን



በ2017 በጀት ዓመት ለአዲስ ዓመት፣ መውሊድ፣ መስቀል እና ኢሬቻ በዓላት የተረጋጋ ገበያ እንዲኖር በመላው ሀገራችን የሚገኙ ኅብረት ስራ ማኅበራት ሰፊ ዝግጅት ሲያደርጉ ቆይተዋል። በተለይም የሸማች ማኅበረሰቡ የሚፈልገውን ምርቶች በበቂ መጠን እና በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት እንዲችሉ በተለያዩ ክልሎች ሰፊ ስራዎች እየተሰሩ ነው፡፡

በኦሮሚያ ክልል ያለውን እንቅስቃሴ ስንመለከት ክልሉ የኅብረት ስራ ኤጀንሲ ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ፣ ከአዲስ አበባ ኅብረት ስራ ኮሚሽን፣ ከኦሮሚያ ንግድ ቢሮ ጋር በመቀናጀት እና ተግባሩን የሚመራ ግብረኃይል በማደራጀት፣ የማስፈፀሚያ እቅድ በማዘጋጀት የተለያየ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለማቅረብ ሰፊ ስራዎችን በማከናወን ላይ ይገኛል፡፡ በመሆኑም ከኦሮሚያ ክልል የተውጣጡ ኅብረት ስራ ማኅበራት በእሁድ ገበያዎች፣ የገበያ ማዕከላት በአዲስ አበባ ከተማ በሚዘጋጁ ኤግዚቢሽን እና ባዛር በመገኘት ምርት ለማቅረብ ሰፊ ዝግጅት በማካሄድ ላይ ይገኛል፡፡ ለበዓሉም በክልሉ የሚገኙ 21 ዩኒየኖች እና 1 ፌደሬሽን 35 724 ኩ/ል የጤፍ ምርት፣ የስንዴ ዱቄት፣ የበቆሎ ዱቄት፣ ቀይ ሽንኩርት፣ ሌሎች አትክልቶች፣ ማር፣ ቡና፣ ቂቤ ለማቅረብ ዝግጅታቸውን አጠናቀዋል፡፡

አማራ ክልል እንዲሁ የምርት አቅርቦቱን አስመልክቶ ከኅብረት ስራ ኤጀንሲው፣ ከንግድ እና ገበያ ልማት ቢሮ እና እንስሳት ሃብት ልማት ቢሮ ጋር በጋራ በመሆን የማስፈፀሚያ እቅድ በማውጣት ወደ ስራ ገብቷል፡፡ ለበዓሉ የሚያስፈልጉ ዋና ዋና የግብርና ምርቶች፣ እንስሳት እና የእንስሳት ተዋፅዖ፣ አትክልት እና ፍራፍሬዎች ጤፍ፣ የስንዴ ዱቄት በገበያ ማረጋጋት ሂደት ለሸማች ማኅበረሰቡ እያቀረበም ይገኛል፡፡ ለበዓሉም በክልሉ በሚገኙ ኅብረት ስራ ማህበራት አማካኝነት 58 ሺህ 176 ኩ/ል የጤፍ፣ ስንዴ ዱቄት፣ ጥሬ በቆሎ፣ ጥራጥሬ፣ አትክልት እና ፍራፍሬዎችን፣ አይብ እና ቂቤ ለማቅረብ ተዘጋጅተዋል፡፡

የማዕከላዊ ኅብረት ስራ ኤጀንሲም በተመሳሳይ በክልሉ የሚገኙ ሁለገብ ኅብረት ስራ ማኅበራት የጤፍ፣ የስንዴ፣ የበቆሎ፣ የአትክልት እና ፍራፍሬ ምርቶችን በሬዎች፣ ፍየሎች፣ አይብ፣ ቅቤ እንቁላል ለሸማች ማኅበረሰቡ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ የሚገኙ ሲሆን ለበዓሉም በክልሉ የሚገኙ 15 ኅብረት ስራ 30 ሺህ 639 ኩ/ል ስንዴ፣ ጤፍ፣ ጥራጥሬ፣ አትክልት እና ፍራፍሬዎችን፣ ቅቤ እና አይብ እንደሚያቀርቡ መረጃ አድርሰውናል፡፡

በሲዳማ ክልልም በተመሳሳይ የምርት አቅርቦቱን አስመልክቶ በክልሉ ከሚገኙ ኅብረት ስራ ዩኒኖች ጋር በተዘጋጀው ማስፈፀሚያ እቅድ ላይ ውይይት የተደረገ ሲሆን ግብይቱንም ተደራሽ ለማድረግ በሃዋሳ ከተማ የኢትዮጵያ የንግድና የዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት በሚያዘጋጀው ኤግዚቢሽን እና ባዛር ላይ በመሳተፍ ለኅብረተሰቡ ምርት ለማቅረብ በዝግጅት ላይ መሆናቸውን መረጃ አድርሰውናል፡ ፡ በዚህም መሰረት ለበዓሉም በክልሉ የሚገኙ 20 ኅብረት ስራ ማኅበራት 500 ኩ/ል ሽንኩርት እና ሌሎች አትክልቶች፣ 1 ሺህ ኩ/ል ጤፍ ፣ 20 ኩ/ል ቅቤ እና አይብ፣ 500 ኩ/ል የስንዴ እና የበቆሎ ዱቄት፣ 10 ኩ/ል የቡላ እና ቆጮ ምርት፣ 5 ኩ/ል ማር ፣ 1000 ሊትር ዘይት፣ 100 የእርድ በሬ፣ ፍየል እና በግ እና 25 ሺህ እንቁላል በቁጥር እንደሚያቀርቡ መረጃ አድርሰውናል፡፡

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኅብረት ስራ ኮሚሽንም እንዲሁ ዝግጅቱን ያጠናቀቀ ሲሆን የ2017 በጀት ዓመት አዲስ ዓመት በዓል አስፈላጊ የሚሆኑ ዋና ዋና ምርቶችን በመለየት ወደ ስራ ገብቷል። ትኩረት የተደረገባቸው ምርቶችና አገልግሎቶች ላይም ዕቅድ በማዘጋጀት አቅርቦቱን በማሳድግ ገበያውን ለማረጋጋት የተግባር ማስፈፀሚያ የሚሆን የግብይት መነሻ ዕቅድ፣ የክትትል፤ ድጋፍ አሰጣጥን አስመልክቶ እቅድ አዘጋጅቶ ከሁሉም ክፍለ ከተማ ጋር የጋራ ያደረገ ሲሆን ለአፈፃፀሙም ስኬታማነት ከኦሮሚያ ኅብረት ስራ ኤጀንሲ፣ ከኦሮሚያ ንግድ ቢሮ እና ከአዲስ አበባ ንግድ ቢሮ ጋር በመቀናጀት እየመራው ይገኛል፡፡

በዚህም መሰረት በኦሮሚያ ክልል ከሚገኙ ኅብረት ስራ ማኅበራት ጋር ትስስር በመፍጠር የጤፍ ምርት፣ የስንዴ እና የበቆሎ ዱቄት በማቅረብ ላይ ይገኛሉ፡፡ በመሆኑም በእቅድ ደረጃ በአስራ አንዱም ክፍለ ከተማ በሚገኙ 11 ዩኒየኖች 23 ሺህ 500 ኩ/ል ጤፍ፣ 16ሺህ ኩ/ል ሽንኩርት፣ 30ሺህ ኩ/ል የበቆሎ እና ስንዴ ዱቄት፣ 525ኩ/ል ገብስ፣ 1 ሺህ 370ኩ/ል ቡና፣ 2 ነጥብ 15 ሚሊየን እንቁላል በቁጥር፤ 325ኩ/ል ቅቤ እና አይብ፣ 2ሺህ በሬዎችን በቁጥር፣ 2 ነጥብ 3 ሚሊየን ሊትር ፈሳሽ ዘይት እና 32ሺህ ኩ/ል ሌሎች ምርቶችን ለማቅረብ በቅንጅት ተግባሩን እየመሩት ይገኛሉ፡፡

ሐረሪ እና ድሬዳዋ ክልልም እንዲሁ ለበዓላት የሚያስፈልጉ የስንዴ ዱቄት፣ ሽንኩርት፣ ቲማቲም በድምሩ 1ሺህ ኩ/ል ምርት እና 100ሺህ ሊትር ዘይት ለማቅረብ በክልላቸው ከሚገኙ ፋብሪካዎች እና አጎራባች ክልሎች ጋር ትስስር የፈጠሩ ሲሆን ምርቱም ለማኅበረሰቡ በከተማው በተቋቋሙ የእሁድ ገበያዎች የሚያቀርቡ ይሆናል፡፡

በፌደራል ደረጃ የተደራጁ ኅብረት ስራ ማኅበራትን በተመለከም በፑሽኪን አደባባይ እንዲሁም በአዲስ አበባ ለሚገኙ የሸማች ኅብረት ስራ ማኅበራት ምርት እያቀረቡ ሸማቹን ተጠቃሚ በማድረግ ላይ ያሉ ሲሆን ለእነኚህ በዓላትም ልዩ ዝግጅት በማድረግ 20ሺህ ኩ/ል የጤፍ፣ ስንዴ፣ የጥራጥሬ፣ አትክልት እና ፍራፍሬዎችን፣ 7ሺህ በግና ፍየሎችን እንዲሁም 450ሺህ እንቁላል በማቅረብ ላይ ናቸው፡፡

በአጠቃላይ በእነኚህ በዓላት ላይ ወደ 220 የሚጠጉ ኅብረት ስራ ማኅበራት ዩኒየኖች፣ ፌደሬሽን እና መሰረታዊ ኅብረት ስራ ማኅበራት በድምሩ 243 ሺህ 593 ኩ/ል የጤፍ፣ የተለያዩ ጥራጥሬዎች፣ ሽንኩርት፣ ሌሎች አትክልቶች እና ፍራፍሬዎች፣ 84 ሺህ 300 ኩ/ል የበቆሎ እና የስንዴ ዱቄት፣ 390 ኩ/ል አይብ እና ቅቤ፣ 25 ኩ/ል ማር እንዲሁም 20ሺህ ዶሮ፣ 2 ነጥብ 73 ሚሊዮን እንቁላል (በቁጥር)፣ 10 ሺህ 666 በሬ፣ በግና ፍየል (በቁጥር)፣ 2ነጥብ 36 ሚሊየን ሊትር ዘይት እና ሌሎች ምርቶች ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ያሉ ሲሆን የሚቀርብበት ዋጋ ከነጋዴው ጋር ሲነፃፀር በዋናነት የስንዴ ዱቄት በኩል ከ1ሺህ 500 እስከ 2ሺህ ብር ልዩነት፣ ቀይ ሽንኩርት 2ሺህ ብር በኩ/ል፣ በሬ ከ10ሺህ እስከ 15 ሺህ በአንድ በሬ፣ ፍየል ከ1ሺህ 500 እስከ 3ሺህ ብር በአንድ ፍየል፣ ሌሎች ምርቶች ከ400 እስከ 500 ብር/ኩል በዋጋ ልዩነት ያላቸው መሆኑን ከኮሚሽኑ ሕብረት ስራ ግብይት መሪ ስራ አስፈፃሚ ያገኘነው መረጃ ያሳያል፡፡

አድራሻ | የኢትዮጵያ ኅብረት ሥራ ኮሚሽን | 0115573448/ 0118592105 | ፖ.ሳ.ቁ. 19787 | Facebook: Ethiopia cooperative Commission | Website: www.fca.gov.et


የኢ.ፌ.ዴ.ሪ. የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ
F.D.R.E. COUNCIL OF CONSTITUTIONAL INQUIRY

# ከኢ.ፌ.ዴ.ሪ የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባኤ
ጋር በመተባበር በየ15 ቀኑ የሚታተም

የሕገ መንግሥት ጉዳዮች አጣሪ ጉባዔ ፅህፈት ቤት እንኳን ለ 2017 አዲስ ዘመን በሰላም አደረሳችሁ እያለ መጪው ዘመን የሰላም የደስታና የብልፅግና እንዲሆንላችሁ ከልብ ይመኛል




አድራሻ፡-
6 ኪሎ ከምስካየ ኅዙናን
መድኃኔዓለም ገዳም ወደ መነን
ትምህርት ቤት በሚወስደው
መንገድ 100 ሜትር ገባ ብሎ
ባለ 5 ወለል ሕንፃ ላይ
ስልክ 011 1 11 68 88/011 1 26 67 24
ፋክስ 011 1 11 68 86
ፌስቡክ WWW.facebook.com/CCIFDRE/
ድረ ገፅ WWW.cci.gov.et
ኢ- ሜይል Constitutionalinquiry.et@gmail.com
Facebook (http://www.facebook.com/CCIFDRE/)
Log in or sign up to view
See posts, photos and more on Facebook.